ኢፕድ
# አዲስ ዘመን
ማክሰኞ
84ኛ ዓመት ቁጥር 021 መስከረም 21 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10.00
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!






# የነጻ ገበያ ሥርዓቱ መደላድል

**ዘላለም ግዛው**

ኢትዮጵያ ሙሉ በሙሉ በነጻ ገበያ ሥርዓት ለመመራት በሽግግር ዋዜማ ላይ ትገኛለች፡፡ በዚህ ወሳኝ ጊዜ መጪውን የገበያ ሁኔታ ማስተዳደር የሚችሉ ተቋማትና ሥርዓቱን መምራት የሚችሉ ብቁ ባለሙያዎች ያስፈልጋሉ፡፡

የመጪው ጊዜ ባለሙያዎች፣ ተቋማት እና የሕግ ማዕቀፉ ምን መምሰል አለባቸው? እንዲሁም የትኞቹስ ተቋማት ቀድመው ሊዘጋጁ ይገባል? የሚለው ፈጣን ምላሽ የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ከነጻ ገበያ ሥርዓቱ ውጪ ልትሆን እንደማትችል፣ ውሳኔውም የዘገየ መሆኑን እና እየተወሰዱ የሚገኙ ውሳኔዎችን ተከትሎ በቂ ዝግጅት ማድረግ እንደሚገባ ዝግጅት ክፍሉ ያነጋገራቸው የሕግ ባለሙያዎች ይናገራሉ፡፡

በኢትዮጵያ የግልግል እና የማስማማት ማዕከል ዳይሬክተር ጠበቃና የሕግ አማካሪው ሚካኤል ተሾመ እንደሚሉት፤ ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የሽያጭ ውሎች በምን አይነት መልኩ መሠራት እንዳለባቸው የሚደነግገውን የኒውዮርክ ስምምነት አፅድቃለች፤ በአዋጅም አውጥታለች፡፡

ወደነጻ ገበያ የሚደረገው ሥራ የተጀመረው እ.አ.አ በ2018 እንደነበር አስታውሰው፤ በቅርቡ ተከታታይ ሕጎች መውጣታቸው እና የውጭ ምንዛሬ ገበያ መር መሆኑ የበለጠ ትኩረት እንዲሰጠው አደረገ እንጂ በቅርበት ለሚከታተለው ቀድሞ የሚገነዘበው ነገር ነው ይላሉ፡፡

ኢትዮጵያ ከነጻ ገበያ ሥርዓቱ ውጪ ልትሆን አትችልም የሚሉት የሕግ አማካሪው ሚካኤል፤ ዓለም አቀፍ የንግድ ድርጅት (WTO) እና የአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና እየመጡ መሆኑን መሠረት በማድረግ ተቋማቱን የሚያንቀሳቅሷቸው ባለሙያዎች ብቁና ዓለም አቀፍ ሁኔታን በመገንዘብ የሚጓዙ መሆን አለባቸው ሲሉ ይመክራሉ፡፡

ጠበቃና የሕግ አማካሪው አቶ ወይናለም ወልደሰንበት በበኩላቸው፤ በኢትዮጵያ በገበያ የሚመራ ሥርዓት ትግበራ በጣም ዘግይቶ የተወሰነ ቢሆንም፤ በመንግሥት እየተወሰዱ

የነጻ ገበያ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# መረጋጋት የተሳነው የአትክልት ገበያ

**ቃልኪዳን አሳዬ እና መስከረም ሰይፉ**

በአዲስ አበባ ከተማ በየቀኑ የሚስተዋለው የሸቀጦች የዋጋ ጭማሪ የኑሮ ውድነቱን ይበልጥ አስቸጋሪ እንዳደረገው ይነገራል፡፡ የምርት አቅራቢዎችና ቸርቻሪዎችም በሀገር ውስጥ ለሚመረቱ የአትክልት ምርቶች እንኳን ሳይቀር ባልተገባ ሁኔታ ዋጋን ከፍና ዝቅ በማድረግ ውጫዊ ምክንያት ሲያስተጋቡ መስማት የተለመደ ሆኗል፡፡

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዘጋቢዎች በአዲስ አበባ ከተማ የአትክልት ዋጋ ምን እንደሚመስል በኮተቤ 02 የገበያ ማዕከል፣ በሾላ ገበያና በተለያዩ የሰንበት መገበያያዎች ተዘዋውረው ቃኝተዋል፡፡

በኮተቤ 02 የገበያ ማዕከል የአትክልት ነጋዴው አለባቸው ፋንታው እንደሚናገሩት፤ የገበያ ሁኔታው ከጊዜ ወደጊዜ በመጨመር ላይ ይገኛል፤ በተለይም በዓላት ሲደርሱ የዋጋ ጭማሪው እየተለመደ መጥቷል፡፡

የጭማሪው ምክንያት ወቅቱ የበዓል ሰሞን ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ፍላጎት በመጨመሩና የአቅርቦት እጥረት በመስተዋሉ መሆኑን ነጋዴው ይገልጻሉ፡፡

እንደ አቶ አለባቸው ገለጻ፤ የገበያው ሰንሰለት በመራዘሙ በመሃል የሚገኙ ደላሎች ያልተገባ የዋጋ ጭማሪ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ ምርቱ እዚህ ከደረሰ በኋላ የወዛደርና ሌሎች ልዩ ልዩ ወጪዎች አሉ፡፡ እንዲሁም የአትክልት ምርቶች በባህሪያቸው የሚበላሹ በመሆናቸው ያንንም ለማካካስ ነጋዴው የዋጋ ጭማሪ ያደርጋል፡፡

መረጋጋት የተሳነው... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# ከቴክኒክና ሙያ ፊት የተደቀኑ እንቅፋቶች

**ሔርሞን ፍቃዱ**

በቀደመው የሥርዓተ ትምህርት ወቅት ወደ መሰናዶ መግባት ያልቻሉ ተማሪዎች በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ተመድበው እንዲማሩ ይደረግ ነበር:: ይህ ሁኔታ ደግሞ ዝቅተኛ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች መሰብሰቢያ ቦታ ነው የሚል አመለካከት እንዲፈጠር በር ከፍቷል:: በአሁኑ በወቅትም የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ውጤት ያላመጡ ተማሪዎች ወደ ዘርፉ ገብተው ለመማር ፍላጎት እንዳይኖራቸው ማድረጉ ይነገራል:: ይህ አመለካከት በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ምን አይነት ተፅዕኖ ይኖረው ይሆን?



ከቴክኒክና ሙያ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



# የአደባባይ በዓላት ለገጽታ ግንባታ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ነው

## - በመዲናዋ በ2017 አንድ ሚሊዮን የውጭ ቱሪስቶችን ለመቀበል ታቅዷል

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- የአደባባይ በዓላት ለገጽታ ግንባታና የልማት ሥራዎችን ለማስተዋወቅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባሕል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ፡፡ በ2017 በጀት ዓመት በመዲናዋ አንድ ሚሊዮን የሚሆኑ የውጭ ሀገር ቱሪስቶችን ለመቀበል መታቀዱ ተመላክቷል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባሕል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሃፍታይ ገብረእግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሀገሪቱ በመስከረም ወር በድምቀት ከሚከበሩ የአደባባይ በዓላት መካከል የመስቀል ደመራ እና የኢሬቻ በዓላት ይገኙበታል፡፡

የመስቀል ደመራ በዓልን ለመታደም ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች ብዙ እንግዶች ተገኝተዋል ያሉት አቶ ሃፍታይ፤ ኢሬቻን በዓል ለመታደም ደግሞ ከሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎችና ከዓለም ሀገራት በርካታ ቁጥር ያላቸው እንግዶች ወደ ከተማዋ ይመጣሉ ብለዋል፡፡

ይህም የከተማዋን ገጽታ ለመገንባት፣ የቱሪዝም ዘርፉን ለማነቃቃት እና አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻዎችና የልማት ሥራዎችን ለማስተዋወቅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የመስቀል ደመራ በዓልን ኢትዮጵያውያን ከአራቱም ማዕዘን የየራሳቸውን የባህል አልባሳትና ጌጣጌጥ ለብሰው እንዲሁም የተለያዩ የዓለም ሀገራት ቱሪስቶች የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች መኖሪያ እና የአንድነት ተምሳሌት



ወደሆነችው አዲስ አበባ በመምጣት ማክበራቸውን አስታውሰዋል፡፡

የመስቀል ደመራ በዓል ለከተማዋ ገጽታ ግንባታና ኢኮኖሚያዊ እድገት ካበረከተው ከፍተኛ አስተዋጽኦ ባለፈ ሕብረ ቀለማችንን፣ ውበታችንንና አንድነታችንን በአደባባይ ለዓለም ሕዝብ አሳይተናል ነው ያሉት፡፡

የአደባባይ በዓላት ሲከበሩ ጫማ ከሚጠርጉ ዜጎች ጀምሮ እስከ ከፍተኛ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ድረስ የኢኮኖሚ አቅማቸውን ከፍ የሚያደርጉበት ሁኔታ እንደሚፈጠር አስታውቀዋል፡፡

በመጪው ቅዳሜ የሚከበረው የኢሬቻ በዓልም በዓለም ከኢትዮጵያውያን አልፎ የዓለም ጸጋ ነው ያሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ በዓሉን ለመታደም ከየትኛውም አቅጣጫ የሚገቡ እንግዶችን በኢትዮጵያዊ የእንግዳ ተቀባይነት ባህል በመቀበል የከተማዋን ገጽታና ኢኮኖሚ ለማሳደግ እየሠራን ነው ብለዋል፡፡

የአደባባይ በዓላት በከተማዋ የተሠሩና እየተሠሩ ያሉ የኮሪደር ልማትን ጨምሮ ሌሎች የልማት ሥራዎችን ለማስተዋወቅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክቱ ገልጸው፤ ኢሬቻን ለማክበር ለሚመጡ እንግዶች ሆቴሎች የምግብ፣ የመኝታ እና የሚጎበኙ ቦታ ጥቅሎችን ለማዘጋጀት እየሠሩ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

ቢሮው ቱሪስቶች ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኙ ለአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ድጋፍና ክትትል የማድረግ ሥራ እንደሚሠራ ጠቁመዋል፡፡

ከተማ አስተዳድሩ ከሰላምና ጸጥታ፣ የበዓሉን እሴት ከማስተዋወቅና ግንዛቤ ከማስጨበጥ አንጻር ከላይ እስከታች ባሉ አደረጃጀቶች በኩል በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ጨምረው ተናግረዋል፡፡

ወጣቶች የአዲስ አበባን በአጭር ጊዜ የመልማት ውጤት አይተውና ተገንዝበው በሚመጡበት አካባቢ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ከተማዋን እንዲጎበኙ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር እየተሠራ መሆኑን አንስተዋል፡፡

ለበዓሉ ተሳታፊዎች በህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጦችን በማሳየትና በመሸጥ እንዲሁም ከተማዋን በማስጎብኘት ሁሉም ርብርብ ሊያደርግ ይገባል ብለዋል፡፡

የኢሬቻ በዓል ሲከበር የከተማው ነዋሪ በእኔነት ስሜት በዓሉን በጋራ እንዲያከብር፣ እንግዶችን በአግባቡ እንዲቀበል እና የከተማዋን ገጽታ ከፍ የሚያደርግ ሥራ እንዲሠራም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በሌላ በኩል በ2017 በጀት ዓመት በመዲናዋ አንድ ሚሊዮን የሚሆኑ የውጭ ሀገር ቱሪስቶችን ለመቀበል ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

# አካዳሚው በበጀት ዓመቱ ከ13 ሺህ በላይ ለሚሆኑ አመራሮችና ባለሙያዎች ሥልጠና ይሰጣል

ማህሌት ብዙነህ

አዲስ አበባ፡- በተያዘው የ2017 በጀት ዓመት ከ13 ሺህ በላይ ለሚሆኑ አመራሮችና ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ሥልጠና ለመስጠት ማቀዱን አዲስ አበባ አመራር አካዳሚ አስታወቀ፡፡

የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ ፕሬዚዳንት ጣሰው ገብሬ (ዶ/ር ) ለኢፕድ እንደገለጹት፤ አካዳሚው የከተማውን የአመራርና የባለሙያውን የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ለማጎልበት እየሠራ ሲሆን በተያዘው ዓመትም ከ 13 ሺህ ስድስት መቶ በላይ ለሚሆኑ አመራሮችና ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ሥልጠና ይሰጣል፡፡

ሥልጠናውም የአመራር ልማትን ትኩረት ያደረገ የዳሰሳ ጥናትን በማዘጋጀት በከተማው ለሚገኙ 5 ሺህ አዳዲስ ተሿሚ አመራሮች፣ ለ2 ሺህ 8 መቶ በላይ ባለሙያዎች፣ ለ5 ሺህ 834 ዳይሬክተሮች የሚሰጥ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

የአቅም ግንባታ ሥልጠናው አገልግሎት አሰጣጥ፣ በመልካም አስተዳደር፣ የችግር አፈታት፣ አዲስ አስተሳሰብና ዘመናዊ አሠራሮችን መከተል እንዲሁም የጥናትና ምርምር ሥራዎች ላይ የሚያተኩር መሆኑን ጠቅሰዋል።

መሪዎች የሥራ አቅጣጫ የሚያስቀምጡና የሚያስተገብሩ ብሎም ውሳኔ የሚያሳልፉ በመሆናቸው ብቃት ያለው የአመራር ክህሎት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለዚህም አካዳሚው በሚሰጠው ሥልጠና የተሰጣቸውን የሕዝብ ተልእኮ በተሻለ እውቀትና ግንዛቤ ለመወጣት ያስችላል ብለዋል፡፡

ዶክተር ጣሰው እንደገለጹት፤ በአካዳሚው የሚሰጡ ሥልጠናዎች ሠልጣኞች መልካም የሥራ ሥነምግባር እና የአገልጋይነት መንፈስ እንዲኖራቸው በማድረግ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚስተዋለውን ችግር በመፍታት የከተማዋን ዘመናዊነትና እድገት የሚመጥን አመራር እና ባለሙያ ለመፍጠር የሚያስችል ነው፡፡



ጣሰው ገብሬ(ዶ/ር)

እስካሁን ባለው ሂደትም አካዳሚው 77 ሺህ በላይ ለሚሆኑ የአመራርና ባለሙያዎች ሥልጠና ከመስጠቱ በተጨማሪ 46 ችግር ፈቺ የጥናትን ምርምር እና ከ7 በላይ የማማከር ሥራዎች የሠራ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

አንድ ተቋም ሊያድግ የሚችለው በአመራሩ ወይም በመሪው ልክ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ለዚህም አካዳሚው የትግበራ ክፍተት በመድፈን እና የሥራ ግልጸኝነት በማስፈን በከተማው በየደረጃው ለሚገኙ አመራሮችና ባለሙያዎች በተሻለ እውቀትና የአቅም ማጎልበት ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል፡፡

እንዲሁም አካዳሚው በተያዘው በጀት ዓመት በከተማዋ ብቁ የሆነ አመራርና ባለሙያ ለመፍጠር እየሰጠ የሚገኘውን ሥልጠና ተደራሽነትና ጥራት ለማሳደግ በተጨማሪ ለከተማው ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምር እንደሚሠራ ዶክተር ጣሰው አስታውቀዋል፡፡

# "አውስትራሊያ ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ሁለንተናዊ ግንኙነት አጠናክራ ትቀጥላለች"

### - ኢቫን ጄ ክሊፎርድ

አማን ረሺድ

አዲስ አበባ፡- አውስትራሊያ ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ስትራቴጂካዊና ሁለንተናዊ ግንኙነት አጠናክራ ትቀጥላለች ሲሉ የአውስትራሊያ ኤምባሲ ሰከንድ ሴክሬተሪ ኢቫን ጄ ክሊፎርድ ገለጹ።

ኢቫን ጄ ክሊፎርድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አውስትራሊያ ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ስትራቴጂካዊ እና ሁሉን አቀፍ አጋርነት ለማስቀጠል ቁርጠኛ ናት።

እንደ ኢቫን ጄ ክሊፎርድ ገለጻ፤ ሁለቱ ሀገራት በግብርና፣ በንግድ፣ ሠብዓዊ ሁኔታ፣ በአየር ንብረት ጉዳዮች እንዲሁም በተለያዩ መስኮች ጠንካራ ግንኙነት አላቸው።

የአውስትራሊያ መንግሥት በምስራቅ አፍሪካ አህጉር የግብርናውን ዘርፍ ለማሻሻል ባለፉት ሁለት ዓመታት ብቻ 40 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ ማድረጉን ገልጸው፤ በዚህም አበረታች ውጤት ተመዝግቧል ብለዋል።

የአውስትራሊያ ባለሀብቶች ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት በግብርና፣ በማዕድንና ቱሪዝም ዘርፍ ኢንቨስት ለማድረግ ፍላጎት እንዳላቸው ኢቫን ጄ ክሊፎርድ ገልጸዋል።

በግብርናው ዘርፍ የሚደረገው ድጋፍ ኢትዮጵያ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የምታደርገውን ጥረት የሚደገፍ መሆኑን አስረድተዋል።

ኢትዮጵያ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ፣ የግብርና መሠረተ ልማት በመገንባት እንዲሁም ሰላምና ደህንነትን በማስጠበቅ ረገድ ለምታደርገው ጥረት አውስትራሊያ እገዛ የምታደርግ መሆኑንም ጠቁመዋል።

ለአብነትም አክስፋም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ የአውስትራሊያ ኩባንያ ሲሆን በምግብ ዋስትና ማረጋገጥ፣ ሠብዓዊና መሰል ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ እንደሚገኝ አመላክተዋል።

በተጨማሪም የአውስትራሊያ የልማት ተራድኦ ፕሮጀክት (ዳፕ) በኢትዮጵያ አነስተኛ ገቢ ያላቸው ማህበረሰብ ክፍሎ ኑሯቸው እንዲሻሻል የዶሮ ዝርያዎችን



በማሰራጨት እገዛ እያደረገ እንደሚገኝ ኢቫን ጄ ክሊፎርድ ተናግረዋል።

በተለይም የኢትዮጵያ ቡና በአውስትራሊያ ዜጎች ተመራጭ መሆኑን አውስተው፤ ይህም ከሀገሪቱ ጋር በንግድ ረገድ ያለውን ዕድል በስፋት ለመጠቀም ያግዛል ብለዋል።

ኢትዮጵያ ወደተሟላ እድገት ለመሻገር በቅርቡ ያደረገችውን የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ የአውስትራሊያ መንግሥት ይደግፋል ያሉት ኢቫን ጄ ክሊፎርድ፤ ባለሀብቶች በኢትዮጵያ የንግድ ሥራ ላይ እንዲሠማሩና የጋራ ተጠቃሚነት እንዲጠናከር ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ገልጸዋል።

አውስትራሊያ ከኢትዮጵያ ጋር ያላት አጋርነት ረጅም ዘመናትን አንዳስቆጠረ አውስተው፤ በቀጣይ በተለይ በኢኮኖሚ ዘርፉ ያላቸውን ትስስር ለማሳደግ የሚያስችሉ ሥራዎች እንደሚሠሩ ጠቁመዋል።

በተመሳሳይ የአውስትራሊያ ኩባንያዎች በኦሮሚያ ክልል በማዕድን ፍለጋ ሥራ ተሰማርተው ይገኛሉ ብለዋል። ከዚህም ባሻገር ከኢትዮጵያ ጋር በትብብር በመሥራት የጋራ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ኢትዮጵያ ጽኑ ፍላጎት እንዳላት ኢቫን ጄ ክሊፎርድ አስረድተዋል።

ዜና



አምባሳደር አይሮሪት መሐመድ (ዶ/ር)

# በአፋር ክልል የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር ምዕራፍ ዛሬ ይጀምራል

**ተስፋ ፈሩ**

ሰመራ፡- የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በአፋር ክልል ከዛሬ ጀምሮ የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር ምዕራፍን እንደሚጀምር ገለፀ፡፡

የአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደቱን አስመልክቶ መግለጫ የሰጡት የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽነር አምባሳደር አይሮሪት መሐመድ (ዶ/ር) እንደተናገሩት፤ በአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደቱ በክልሉ የሚገኙ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በአጀንዳ ሃሳቦቻቸው ላይ ውይይት የሚያደርጉ ሲሆን፣ በተጨማሪም ኮሚሽኑ በሀገራዊ ምክክር ጉባዔ ላይ ተሳታፊ የሚሆኑ የክልሉን ወኪሎች ያስመርጣል፡፡

ኮሚሽኑ ከዚህ ቀደም በክልሉ ከሚገኙ ወረዳዎች የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን የሚወክሉ ተወካዮችን በአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት እንዲሳተፉ አስመርጦ ማዘጋጀቱን ያወሱት ኮሚሽነሯ፤ በመጪዎቹ ሁለት ቀናት እነዚህ የሕብረተሰብ ክፍል ወኪሎች በአጀንዳ ሃሳቦቻቸው ላይ በየቡድናቸው ተወያይተው የተስማሙባቸው አጀንዳዎች ወደ ቀጣዩ የምክክር መድረክ ለሚያቀርቡላቸው ተወካዮቻቸው በአደራ ይሰጣሉ ብለዋል፡፡

ሂደቱ በሚከናወንባቸው ሶስተኛ፣ አራተኛ እና አምስተኛ ቀናት ከላይ የተጠቀሱትን የሕብረተሰብ ክፍል ወኪሎችን ጨምሮ በክልሉ የሚገኙ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በወኪሎቻቸው አማካኝነት የአጀንዳ ሃሳቦቻቸው ላይ በቡድን እንደሚወያዩና የተስማሙባቸውን አጀንዳዎችም በሚመርጧቸው ተወካዮቻቸው አማካኝነት እንደሚያቀርቡ ነው ኮሚሽነሯ የገለፁት፡፡

ከነገ ማክሰኞ መስከረም 21 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ ለስድስት ተከታታይ ቀናት በሚከናወነው የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር ምዕራፍ መድረክ በአፋር ክልል ከሚገኙ ከ49 ወረዳዎች የተመረጡ ከ800 በላይ የሕብረተሰብ ክፍል ወኪሎች እንዲሁም ከ700 በላይ በክልሉ የሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮች፣ የሶስቱ የመንግሥት አካላት ተወካዮች ተወካዮች፣ በክልሉ የሚገኙ የተለያዩ ተቋማትና ማህበራት ተወካዮች እንዲሁም በክልሉ የሚኖሩ ተፅእኖ ፈጣሪ ግለሰቦች ተሳታፊዎች እንደሚሆኑም አመላክተዋል፡፡

ይህ መርሃግብር የአፋር ክልል የሕብረተሰብ ክፍል ተወካዮች እና ባለድርሻ አካላት ሀገራዊ መግባባት ሊደረግባቸው ይገባል የሚሏቸውን እጅግ መሠረታዊ ሀገራዊ ጉዳዮችን የያዙ አጀንዳዎች በሕዝባዊ ውይይት የሚያዳብሩበት ብሎም ለኮሚሽኑ የሚያቀርቡበት ወሳኝ ምዕራፍ በመሆኑ የሁሉም ባለድርሻ አካላት ንቁ ተሳትፎ በእጅጉ ወሳኝ መሆኑንም ኮሚሽነሯ ተናግረዋል፡፡

የባለድርሻ አካላት ተወካዮች በክልሉ ለተከታታይ ስድስት ቀናት የሚደገረውን የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር ምዕራፍ ክልላዊና ሀገራዊ ፋይዳውን በመረዳት ንቁ ተሳትፎን ለማድረግ እንዲዘጋጁና በሂደቱም የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉም ኮሚሽነሯ ጥሪ አስተላልፈዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ከግንቦት 21 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ የክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር መድረኮችን በተከታታይ እያካሄደ ይገኛል።

# "ኢትዮጵያ በጀመረችው ፈጣን እድገት ልክ ለመጓዝ ለሙያና ሙያተኞች ተገቢው እውቅና ይሰጣል"

- ሙፈሪያት ካሚል
የሥራና ክሂሎት ሚኒስትር

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ከጀመረችው ፈጣን እድገት እኩል ለመጓዝ ለሙያና ሙያተኞች ተገቢውን ክብርና እውቅና እንደሚሰጥ የሥራና ክሂሎት ሚኒስትር ወይዘሮ ሙፈሪያት ካሚል ገለጹ። በኢትዮጵያ በልምድ ለተገኘ ክሂሎት እውቅና መስጠት ተጀምሯል።

ሚኒስትሯ "በልምድ ለተገኘ ብቃት" የእውቅና አሰጣጥ ማስጀመሪያ መርሀ ግብር ትናንት በተካሄደበት ወቅት፣ በትኛውም መንገድ የተገኘ ክህሎት እውቅና ሲሰጠው በውጤት የታጀበ ትልቅ ማህበረሰብ ለመገንባት ያስችላል ብለዋል።

እንደ ማህበረሰብ የተፈጠረው አቅም ተመልሶ እንደ ሀገር ኢኮኖሚው ያለውን ፍላጐትና አቅርቦት ለማጥበብና በሂደትም ለመፍታት ትልቅ አቅም እንደሆነ ጠቅሰው፣ ኢትዮጵያ ከጀመረችው ፈጣን እድገት እኩል ለመጓዝ ለሙያና ሙያተኞች ተገቢውን እውቅና እንደሚሰጥ አስታውቀዋል።

ብዙ ክህሎት ያላቸው ዜጐች ለኢኮኖሚው እድገትና ተወዳዳሪነት ያላቸው ሚና ትልቅ ነው ያሉት ሚኒስትሯ፣ ለሙያ ክብር መስጠት ሀገራዊ ተወዳዳሪነትን እና ምርትና ምርታማነት ከማሳደግ አኳያ ፋይዳው የላቀ መሆኑን ጠቁመዋል።

ለኢ. መደበኛ ክህሎት እውቅና የመስጠቱ ሥራ እድሜ፣ ጾታ፣ የአካል ጉዳት፣ ሃይማኖትና ሌሎች ጉዳዮችም ድንበር ሳይኖራቸው መላው ኢትዮጵያውያንን ተደራሽ እንደሚያደርግ ገልጸዋል። በተለይም



በኮንስትራክሽን፣ በእደ ጥበብ፣ በኤሌክትሮኒክስና መሰል ዘርፎች በኢ-መደበኛ መንገድ ለተገኙ ክህሎቶች እውቅና መስጠትና ወደ መደበኛ ክህሎት ማሻገር እንደሚገባ ጠቅሰዋል።

ወደ መደበኛው ኢኮኖሚ የሚመጣው የሰው ሃይል ከእነዚህ ዜጐች የተውጣጡትንም ይጨምራል ሲሉ ተናግረዋል።

በኢ. መደበኛ መንገድ ክህሎት ያገኙትን ዜጐች ብቃት ለመገምገም እና እውቅና ለመስጠት የማስተግበሪያ መመሪያ መዘጋጀቱን ተናግረው፣ ይህም ለነባር እውቀታቸው፣ ችሎታቸው እና ልምዳቸው እውቅና እንዲያገኙ ያስችላቸዋል ነው ያሉት። የማስተግበሪያ መምሪያው ኢትዮጵያ ለጀመረችው ልማት ከፍተኛ ድርሻ እንዳለውም ጠቅሰዋል።

ክህሎት ያለው ዜጋ ቁጥር ሲጨምር ምርታማነትም በዛው ልክ እያደገ ስለሚመጣ ይህ አይነቱ አሠራር ሙያተኞችንና የግል ዘርፉን ተጠቃሚ የሚያደርግ ሥርዓት ነው ብለዋል።

ዜጐች በራስ የመተማመን ብቃታቸው እያደገ እንዲመጣና የመደራደር አቅማቸውን እንዲያድግ ትልቅ ሚና ያለው እንደሆነም ተናግረዋል

እንደ ሚኒትሯ ገለጻ፣ ኢትዮጵያ የጀመረችው ጉዞ ፈጣን፣ ፋታ የማይሰጥ፣ አካታች ሲሆን፣ ሁሉንም ዜጋ በተሳትፎው ልክ ተጠቃሚ ማድረግ ከሚያስችለው የኢኮኖሚ እድገት ጋር መጓዝ ካልተቻለ፣ እንዲሁም ያሉ አቅሞችን በአግባቡ ማምጣት የሚያስችል እድል መፍጠር ካልተቻለ፣ ሀገር ያላትን አቅም በሙሉ አሟጦ ማልማት የሚያስችል ምቹ ሁኔታ እውን ማድረግ ያስቸግራል። ስለዚህም ኢትዮጵያ ከጀመረችው ፈጣን እድገት እኩል ለመጓዝ ለሙያና ሙያተኞች ተገቢው እውቅና የመስጠቱ ሂደት ተጠናክሮ ይቀጥላል።

# ተመድ፤ ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል እያከናወነች ላለው ተግባር ድጋፉን አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታወቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የልማት መርሃ-ግብር (ዩ ኤን ዲ ፒ) ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል እያከናወነች ላለው ተግባር ድጋፉን አጠናክሮ እንደሚቀጥል ገለጸ።

በኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖን የሚቋቋም አረንጓዴ ኢኮኖሚን ለመገንባት በሚከናወኑ ተግባራት ላይ የሚመክር የባለድርሻ አካላት የባለሙያዎች ፎረም ዛሬ ተካሂዷል።

የፎረሙ ሰብሳቢ የፕላንና ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ስዩም መኮንን፤ ፎረሙ ኢትዮጵያ የአረንጓዴ ምጣኔ ሀብት ልማትን ለመገንባት የምታደርገውን ጥረት እውን ለማድረግ የሚያስችል ትብብር ለመፍጠር ያስችላል ብለዋል።

ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል ለምታዘጋጃቸው ፖሊሲና ስትራቴጂዎች በተለይም የቴክኒክ፣ የፋይናንስና ሌሎች የዘርፉን ዓለም አቀፍ ልምዶች በማምጣት በትብብር ለመሥራት ዕድል እንደሚፈጥርም ገልፀዋል።

ዓለም አቀፍ ተቋማት ትብብራቸውንና የፋይናንስ ድጋፋቸውን በዘላቂነት እንዲያጠናክሩ ዕድል ይፈጥራልም ነው ያሉት። በቀጣይም ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል በብሔራዊ ደረጃ ለምትተገብረው ዕቅድ የሚያስፈልገውን ፋይናንስ ለመሸፈን የልማት አጋሮች ሚና ከፍተኛ መሆኑን ገልፀዋል።

ዕቅዱን ለመተግበር ለአሥር ዓመት 316 ቢሊዮን ዶላር የሚያስፈልግ ሲሆን፤ 253 ቢሊዮን ዶላር ከዓለም አቀፍ የልማት አጋሮች የሚገኝ በመሆኑ ትብብራቸውን



ሳሙኤል ዶ



አቶ ስዩም መኮንን

እንዲያጠናክሩ ጥሪ አቅርበዋል።

የፎረሙ ጸሐፊ የተባበሩት መንግሥታት የልማት መርሃ-ግብር (ዩ ኤን ዲ ፒ) የኢትዮጵያ ተወካይ ሳሙኤል ዶ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል በአረንጓዴ ዐሻራና ሌሎች ዕቅዶች የምታከናውነው ተግባር የሚደነቅ መሆኑን ገልፀዋል።

ዩ ኤን ዲ ፒ ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥን በመከላከል አረንጓዴ ልማትን ለመገንባት የያዘችውን ዕቅድ እውን ለማድረግ ዓለም አቀፍ ተቋማትን በማስተባበር ድጋፋቸውን እንደሚቀጥሉ አረጋግጠዋል።

የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖን የሚቋቋም አረንጓዴ ምጣኔ ሀብት ለመገንባት በሚከናወኑ የባለሙያዎች ፎረሙ፤ በኢትዮጵያ በአየር ንብረት ለውጥና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ የሚሠሩ ዓለም አቀፍ የልማት አጋሮችና የመንግሥት ተቋማት በአንድነት የሚሠሩበት ነው።

እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ2011 የተቋቋመ ሲሆን፤ በየሦስት ወሩ በመገናኘት በኢትዮጵያ በአየር ንብረት ለውጥ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ትግበራ ላይ ውይይት በማድረግ የአፈጻጸም አቅም የሚያጠናክር ነው።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የናይል ትብብር ማዕቀፍ ወደ ሕግነት የመሻገሩ ሂደት ለተፋሰሱ ሀገራት አዲስ የትብብር ምዕራፍ የሚከፍት ነው!

የናይል ወንዝ ውሃ አጠቃቀምን ፍትሃዊ ለማድረግ እና በመካከላቸው ያለውን ትብብር ለማሳደግ የተፋሰሱ ሀገራት "የናይል ተፋሰስ ሀገራት የትብብር ማእቀፍ "ቀርፀው ለተግባራዊነቱ ለዓመታት ሲንቀሳቀቀሱ ቆይተዋል። ከብዙ ፈተናዎች እና ውጣ ውረዶች በኋላም ማዕቀፉ አሁን ላይ ገዥ ሕግ የሚሆንበት ታሪካዊ ምዕራፍ ላይ ደርሷል።

የናይል ወንዝ ውሃ አጠቃቀም ለረጅም ዘመናት በተፋሰሱ ሀገራት መካከል ያለመግባባት ምክንያት እና ለተፋሰሱ ሀገራት የጸጥታ እና ያለመረጋጋት ምንጭ ሆኖ እስካሁን መዝለቁ የአደባባይ ሚስጥር ነው። በዚህም አብዛኞቹ የተፋሰሱ ሀገራት በአንድም ይሁን በሌላ ከወንዙ ውሃ ጋር በተያያዘ በተፈጠሩ የተዛቡ አስተሳሰቦች ያልተገባ ዋጋ ለመክፈል ተገድደዋል።

በችግሩ ምንጭነት በዋንኛነት የሚጠቀሱት ቅኝ ገዥዎች በወንዙ ውሃ የነበራቸውን ጥቅሞች ለማስጠበቅ ሲሉ በተለያዩ ወቅቶች ያስቀመጧቸው ኢፍትሃዊ የውሃ አጠቃቀም ውሎች ናቸው ። ውሎቹ ከቅኝ ገዥዎች የተዛባ አመለካከት የተቀዱ ፤ የተፋሰሱን ሀገራት ሕዝቦች ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ታሳቢ ያላደረጉ ፤ አሁን ላይ ያሉ ዓለም አቀፍ ሕጎችን እና የሞራል እሳቤዎችን ከግምት ውስጥ ያላስገቡ ፤ የቀደሙትን የአፍሪካውያን የነጻነት ትግል እና በትግሉ የተካፈሉ መስዋዕትነቶችን የሚያሳንሱ ናቸው።

በነጻነት ማግስት አፍሪካውያን የጋራ ዕጣ ፈንታቸውን ለመቅረጽ ያስችላቸው ዘንድ ተግባራዊ ካደረጉት የፖለቲካ ኢኮኖሚ / የፓን አፍሪካኒዝምን እሳቤ የሚቃረኑ ፤ ከቅኝ ገዥዎች አስተሳሰብ እና አስተሳሰቡ ሊፈጥር የሚችለውን ያልተገባ ተጠቃሚነትን ለማስቀጠል የሚሞክሩ ዘመኑን እና የዘመኑን አስተሳሰብ የማይሸከሙ የአፍሪካዊ ወንድማማችነት ጠረን የሌላቸው ናቸው።

እነዚህን ከዘመኑ ጋር አብሮ የማይሄድ ውሎችን በመግራት ፍትሃዊነትን መሠረት ያደረገ የወንዝ ውሃ አጠቃቀም እና ከዚህ የሚመነጭ የትብብር ማዕቀፍ ተግባራዊ ለማድረግ ላለፉት ሁለት አስርት ዓመታት የተፋሰሱ ሀገራት በብዙ ፈተናዎች የተሞሉ ተደጋጋሚ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል።

አንዳንድ የተፋሰሱ ሀገራት ውሎቹን እንደ ተፈጥሯዊ መብት በመቁጠር ፤ የሀገራትን በውሃው በፍትሃዊነት የመጠቀም መብት የሚገዳደሩ አስተሳሰቦችን በስፋት በማራመድ ፤ ከቅኝ ግዛት ውሎቹ በስተጀርባ ያለውን የቅኝ ገዥዎች የተዛባ አስተሳሰብ ዛሬ ላይ ሕይወት እንዲዘራ ብዙ ተጉዘዋል።

የወንዙ ውሃ በፍትሃዊ ተጠቀሚነት መርህ ተገዥ በሆነ አስተሳሰብ ከተገራ የተፋሰሱን ሀገራት ሕዝቦችን የጋራ ተጠቃሚነትን በማስፈን ሂደት ውስጥ የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንደሆነ ይታመናል። በሀገራቱ መካከል አንድ የትብብር አቅም በመሆን ቀጣይ በሆነው ግንኙነታቸው ላይ ሊኖረው የሚችለው አስተዋጽኦም ከፍ ያለ ነው።

ይህ ሊሆን የሚችለው ግን በወንዙ ውሃ አጠቃቀም ዙሪያ ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን መሠረት ያደረገ በመርህ የሚገዛ ፤ ከሁሉም በላይ በሀገራቱ መካካል መተማመንን የሚፈጥር የጋራ አስተሳሰብ እና ለአስተሳሰቡ ገዥ መሆን የሚያስችል ቁርጠኝነት መፍጠር ሲቻል ብቻ ነው።

"የናይል ተፋሰስ ሀገራት የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት "ያስፈለገውም ይህንኑ እውነታ ተጨባጭ ለማድረግ ነው። ኢትዮጵያ፣ ታንዛኒያ ፣ ሩዋንዳ ፣ ኡጋንዳ ፣ ብሩንዲ እና ደቡብ ሱዳን ማዕቀፉ አሁን የደረሰበት ታሪካዊ ምዕራፍ ላይ እንዲደርስ ያሳዩት ቁርጠኝነትም የዚህ እውነታ ተጨባጭ ማሳያ ተደርጎ የሚወሰድ ነው ።

የሀገራቱ ውሳኔ ለፍትሃዊ ተጠቃሚነት ያላቸውን ቁርጠኝነት ከማሳየት ባለፈ ፤ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ሊያመጣ የሚችለውን አዲስ የትብብር ምዕራፍ በአግባቡ መረዳታቸውን የሚያረጋግጥ ፤ የወንዙ ውሃ የግጭት እና ያለመግባባት ምንጭ ከመሆን ወጥቶ የትብብር እና የወዳጅነት ምንጭ እንዲሆን ያላቸውን ቀናነት ማረጋገጫ ነው።

ውሳኔያቸው የተፋሰሱን ሀገራት ከግጭት ወደ ትብብር ፤ ካለመተማመን ወደ መተማመን ፤ የሚመልስ ሀገራት በወንዙ ውሃ አጠቃቀም ዙሪያ በኃላፊነት እና በተጠያቂነት እንዲንቀሳቀሱ የሚያስችል ነው ። ሀገራቱን በፍትሃዊነት ዙሪያ የአንድ ታሪካዊ ድል ባለቤት የሚያደርግ ፤ ዓለም አቀፍ እውቅና የሚሰጠው ትልቅ ውሳኔ ነው!


## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የእሁድ ገበያው ዓላማውን እንዳይስት!

በኃይሉ አበራ

በሀገሪቱ በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ በግብርናና በኢንዱስትሪ ምርቶች ላይ ሲታይ የነበረውን የዋጋ ጭማሪ ተከትሎ የኑሮ ውድነቱም ሲባባስ ቆይቷል። ለእዚህ የዋጋ መጨመር በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች ሊኖሩ ቢችሉም፣ የደላሎችና ሕገወጥ ነጋዴዎች የሚፈጽሙት ሕገወጥ ተግባር ግን በዋና ምክንያትነት ይጠቀሳሉ።

መንግሥትም ይህ የኑሮ ውድነት በህብረተሰቡ ላይ ጫና እንዳያሳድር ለማድረግ ገበያ የሚያረጋጉ ርምጃዎችን ሲወስድ መቆየቱ ይታወቃል። ሕገወጥ ግብይትን በመቆጣጠር እንዲሁም አቅርቦት ላይ በመሥራት ገበያውን ለማረጋጋት ከመሞከሩ በተጨማሪ በፍጆታ ምርቶች ላይ ድጎማ በማድረግ በሸማቾች ማህበራት በኩል ለህብረተሰቡ እንዲደርሱ አድርጓል።

በዚህ ብቻም ሳይወሰን የእሁድ ገበያዎችንም ለእዚህ ዓላማ በማዋል የአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም እንደ ዱቄት ያሉት የኢንዱስትሪ ምርቶች ለህብረተሰቡ በየአቅራቢያው በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲደርሱ ለማድረግ ሠርቷል።

በእነዚህ ጥረቶች በተለይ በሸማቾች ማኅበራት በኩል ዘይትና ስኳር እንዲሁም የዳቦ ዱቄት በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲደርሱ ተደርጓል። በየበዓላቱም የዘይትና የመሳሰሉት የፍጆታ ምርቶችን በእነዚህ ማህበራት በኩል በማቅረብ ገበያውን ለማረጋጋት ተሞክሯል።

በሌማት ትሩፋት እና የከተማ ግብርና ሥራዎችም እንዲሁ እንደ እንቁላል፣ ዶሮና ወተትና የወተት ተዋጽኦዎችን በማምረት ለገበያ ለማቅረብ ተሠርቷል፤ እየተሠራም ነው።

በተለይ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በከተማዋ መግቢያ በሮች ላይ አምስት የግብርና ምርቶች የግብይት ማእከላትን በመገንባት ህብረተሰቡ ከአምራቾች በቀጥታ የግብርና ምርቶችን የሚገዛበትን ሁኔታ ፈጥሯል። ይህ ሂደት የደላላውን እጅ በመቁረጥ የረዘመውን የገበያ ሰንሰለት በማሳጠር የግብርና ምርቶች በተመጣጣኝ ዋጋ ህብረተሰቡ ዘንድ እንዲደርሱ እያስቻለ መሆኑ ይገለጻል።

የኑሮ ውድነትን ለመቀነስ ወይም ዋጋን ለማረጋጋት እየተሠራባቸው ከሚገኙት መካከል የእሁድ ገበያዎች (ቅዳሜም ጭምር ይካሄዳሉ) ይጠቀሳሉ። በ2014 ዓ.ም መጀመሪያ አካባቢ የዋጋ ንረት ለማረጋጋትና ጤናማ የግብይት ሥርዓትን ለመዘርጋት አምራች ህብረት ሥራ ዮኒየኖችን ከአዲስ አበባ ከተማ ሸማች ህብረት ሥራ ማህበራት ጋር በማቀናጀት ዋጋ በማረጋጋት ሥራ እንዲሠማሩ የተደረጉት ሳምንታዊዎቹ የእሁድ ገበያዎች፣ በሂደት እየተስፋፉ እንዲመጡ ተደርጓል፤ ቅዳሜንም ጨምሮ አገልግሎት ወደ መስጠት እንዲሸጋገሩ መደረጉ ይታወቃል።

በወቅቱ ማህበረሰቡ እነዚህን ዋጋን ለማረጋጋት እና አማራጭ የፍጆታ ምርቶችን የሚያገኝባቸው ሁኔታዎች በመፈጠራቸው ደስታውን ሲገልጽም ነበር። አጀማመራቸው ጥሩ እንደመሆኑም የህብረተሰቡ አስተያየት ተገቢ ነበር ብሎ መውሰድ ይቻላል። የቅዳሜና እሁድ ገበያ የሚካሄድባቸው ቦታዎች በአንድ በኩል እየሰፉ መምጣታቸው በአዎንታዊነት ቢወሰድም፣ ህብረተሰቡ በገበያዎች በስፋት የሚታይበት ሁኔታ ሲታይ ገበያዎቹ ህብረተሰቡን ያማከሉ ናቸው ብሎ ቢወሰድም ችግር አልነበረባቸውም፤ የለባቸውም ግን አይባልም።

በአሁኑ ወቅት የእሁድ ገበያዎች እንደ አጀማመራቸው ሥራቸውን እየሠሩ ነው ወይ ተብሎ ሲጠየቅ ምላሹ አይደለም የሚል ሆኗል። ገበያን በማረጋጋት በኩል ሃላፊነታቸውን እየተወጡ አለመሆናቸው በሰፊው እየተጠቆመ ነው። በዋጋም በምርት ጥራት በኩልም ቅሬታ እየቀረበባቸው ይገኛሉ።

በገበያዎቹ ህብረተሰቡ የሚፈልጋቸው ምርቶች ተለይተው በበቂ ሁኔታ እየቀረቡ ስላለመሆናቸው ቅሬታዎች ይቀርባሉ። በእነዚህ ገበያዎች በብዛት የሚቀርቡት የግብርና ምርቶች ጥሩ ቢሆንም፣ ምርቶቹ በዋጋም በጥራትም አጠያያቂ እየሆኑ የመጡበት ሁኔታ ግን ዓላማቸውን እያሳኩ አለመሆናቸውን ያመለክታል። በገበያው የሚቀርቡት ምርቶች በአብዛኛው ጥራት የጎደላቸው፣ ዋጋቸውም ከሌላው አካባቢ/ በአቅራቢያቸው ከሚገኙ መደብሮች ዋጋ/ እምብዛም ልዩነት የሌለው ነው እየተባለ ይገኛል፤ የሚያቀርቧቸው እንደ ቲማቲም ያሉት ምርቶችም ቢሆኑ በሌላ ቦታ ፈላጊ ያጡ በአብዛኛው ጠባሳ ያለባቸው፣ የሸንኩርት ምርቶችም እንዲሁ ችግር ያለባቸው መሆናቸው ይገለጻል።

ገበያዎቹ አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የፍጆታ ምርቶችን በስፋት መያዝ ሲገባቸው የኢንዱስትሪ ምርቶችን በብዛት ይዘው የሚታዩበት ሁኔታም ዓላማቸውን እየሳቱ ናቸው የሚያሰኛቸው ነው።

ገበያዎቹ የምርቶቹን ዋጋ ዝርዝር በሚሸጡባቸው ድንኳኖች ላይ በግልጽ ቦታ፣ በጉልህ ጽፈው በሚታይ ሥፍራ መለጠፍ ሲገባቸው ይህን ባግባቡ አያደርጉም። አንደኛ በጉልህ አይጽፉም፤ ሁለተኛ ማንኛውም ሸማች ሊያይ በሚችልበት ቦታ ላይ አይለጥፉም። ለይስሙላ ያንን ዝርዝር ለጥፈው፣ የሚሸጡት በመደበኛው ገበያ ወይም ከዚያ ብዙም ባልተለየ ዋጋ ነው። በዚህ የተነሳም ህብረተሰቡ የዚህ የዚህ ለምን ከመደበኛው ገበያ አልገዛም ብሎ ትቶ የሚሄድበት ሁነታ አለ እየተባለ ነው።

የእነሱ ጉድ የሚወጣው ባግባቡ የሚሠሩ ተቆጣጣሪዎቻቸው ሲመጡ ብቻ ነው። እነሱ የመጡ ጊዜ በለጠፉት ዋጋ መሠረት ይሸጣሉ። እነሱ ዞር ሲሉ ደግሞ በፈለጉት ዋጋ ይሸጣሉ። ገበያው የልጅነት ጨዋታው የሌባና ፖሊስ አይነት ሆኗል።

ህብረተሰቡም ስለገበያዎቹ በቂ ግንዛቤ ያለው አይመስልም። ድንኳኑ ላይ የተለጠፈውን የዋጋ ዝርዝር የሚያውቁት እጅግ ጥቂት የሚባለው ሸማች ብቻ ነው። በአጋጣሚ ተቆጣጣሪዎች ሲመጡ ዝርዝሩን ካላዩ በስተቀር የማያውቁት ይበረከታሉ። ዋጋውን ቢያውቁትም በዚያ ዋጋ የሚሸጥላቸው ማግኘታቸውም ያጠራጥራል።

ከዚህ መረዳት የሚቻለው ነጋዴዎች የዋጋና ምርት ዝርዝሩን በጉልህ ጽፈው የሚታይ ሥፍራ ላይ እንዲለጥፉ ማድረግ የሚያስፈልግ መሆኑን ነው፤ ይህን በማያደርጉት ላይም አስተማሪ ርምጃ መውሰድም ይገባል።

ህብረተሰቡም በገበያዎቹ ዓላማና በአሠራሩ ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው ማድረግም ተገቢ ይመስለኛል። ህብረተሰቡ በገበያው ዋጋ መሠረት ምርቶቹን እንዲገዛ ለማድረግ የቁጥጥር ሥራው ወሳኝ ይሆናል። መንግሥት ለህብረተሰቡ ሲል የፈጠራቸው ገበያዎች የሕገወጦች ምሽግ እንዳይሆን በማድረግ በኩል የገበያው ዋንኛ ተጠቃሚ መሆን የሚገባው ህብረተሰቡ እንደመሆኑ ተባባሪ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል።

ህብረተሰቡ ገበያዎቹን እንደሚፈልጋቸው ይታወቃል። ገበያዎቹ ላይ የሚታየው ትርምስም ይህንኑ ይጠቁማል። የእሁድ ገበያ ነጋዴዎች ጥራት የሌለው ምርት ይዘው፣ ከመደበኛው ገበያ ዋጋ ብዙም ልዩነት ሳያደርጉ እየሸጡ ባሉበት ሁኔታም ገበያዎቹ ጭር ብለው አያውቁም። ይህ ሁሉ እየሆነም አዳዲስ ገበያዎች እየተፈጠሩ ናቸው፤ ከስረው የዘጉ የሉም።

ከዚህ መረዳት የሚቻለው ገበያዎቹ እንደሚያስፈልጉ ነው። እነዚህ ገበያዎች መበራከታቸውም ሆነ መቆየታቸው አስላጊነታቸውን ይጠቁማል። ህልውና የሚኖራቸው ግን ህብረተሰቡን ያማከለ ግብይት ሲያካሂዱ ብቻ መሆኑ መታወቅ አለበት። ነጋዴዎቹም ገዥ ማግኘታቸውን እንደ ጤናማ ሥራ መመልከት አይገባቸውም። ገበያው የተፈቀደበትን ዓላማ በሚያሳካ መልኩ ነው መሥራት አለባቸው።

የመንግሥት አካላትም የቁጥጥር ሥራቸውን ማጠናከር አለባቸው። በግብይት ሥፍራው ባስቀመጡት የዋጋ ዝርዝር መሠረት ስለመሸጥ አለመሸጣቸው በተለያዩ መንገዶች ክትትል መደረግ ይኖርበታል፤ በቂ የምርት አቅርቦት ስለመኖሩም እንዲሁ ክትትል የሚደረግበት ሊኖር ይገባል።

በቅዳሜና እሁድ ገበያ ቦታዎቹ ማሊያ ቀይረው የሚጫወቱ እንዳሉም ይገለጻል። ባለ ትላልቅ መደብሮችም በድንኳኖቹ ገብተው ሲሸጡ ማየት ተለምዷል። ይሄም ሌላው ሕገወጥነት ነው። እነዚህ ነጋዴዎች ህብረተሰቡን ከመጉዳት ባሻገርም የእሁድ ገበያዎቹን ነጋዴዎች በሕገወጥ ተግባራቸው አይበክሉም ተብሎ አይታሰብም። በእነዚህ ላይም ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግና ከገበያው ማስወጣት ያስፈልጋል።

ህብረተሰቡም የተቀመጠውን የዋጋ ዝርዝር በማየት በተቀመጠው ዋጋ መሠረት ሲገዛ አይታይም። በዚህ በኩል ህብረተሰቡ በቂ ገንዛቤ እንዲኖረው የተደረገም አይመስለኝም። ይህ ሁኔታና ነጋዴዎች የሚፈጽሙት ሕገወጥ ተግባር ሲታይ የሚመለከተው የቁጥጥር አካል ዋጋው በግልጽ እንዲታይ ማድረግ እንዲሁም ገበያውን የማረጋጋት ሥራው በትክክል ሥራ ላይ ስለመዋሉ የመቆጣጠር ሃላፊነቱን እየተወጣ ነው ማለት ያስቸግራል። የእሁድ ገበያው ዓላማውን እንዳይስት መደረግ ይኖርበታል!

# መረጋጋት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ነገር ግን ካለፈው ይልቅ የተወሰኑ መሻሻሎች እየታዩ መሆናቸውን የሚያነሱት አቶ አለባቸው፤ ባለፉት ቀናት የሽንኩርት ዋጋ እስከ 140 ብር የነበረ ቢሆንም አሁን ላይ ከ90 ብር እስከ 120 ብር፣ ቲማቲም ከ60 ብር እስከ 70 ብር፣ እንዲሁም ድንች በአማካይ 25 ብር እየተሸጠ ይገኛል ይላሉ፡፡

ችግሩን ለመፍታት በተለይም በሀገሪቱ ተግባራዊ እየተደረገ ያለው የነጻ ገበያ ሥርዓት በመሆኑ አቅርቦትን በመጨመር ከፍላጎት ጋር ማጣጣም እንዲሁም የግብይት ሰንሰለቱን ማሳጠር እና ሰላም ማስፈንም ለነገ የማይባል መሆኑን አቶ አለባቸው ያነሳሉ፡፡

በኮተቤ 02 የገበያ ማዕከል ሲሸምቱ ያገኘናቸው አቶ በላይ ቸሩ እንደሚገልጹት፤ በገበያዎች ላይ እየታየ የሚገኘውን ድንገተኛና ጊዜውን ያልጠበቀ የዋጋ ጭማሪ የሚቆጣጠረው አካል በማጣቱ አነስተኛ ገቢ ያላቸው ዜጎች ሕይወታቸውን በአግባቡ መምራት አቅቷቸዋል፡፡

ለቤት አስቤዛ የሚሆኑ የሽንኩርት፣ ቲማቲም፣ ድንችና ሌሎች የአትክልት አይነቶችን ለመሸመት ወደገበያ መምጣታቸውን በመግለጽ፤ በገበያው ላይ ነጋዴዎች የሚጠሩት ዋጋ ያሰቡትን ያህል ሊያስሸምታቸው እንዳልቻለ አቶ በላይ ይጠቁማሉ፡፡

የመስከረም ወር የበዓል ወቅት በመሆኑ በሁሉም ምርቶች ላይ የሚታየው የዋጋ ጭማሪ አሳሳቢ ሆኗል የሚሉት አቶ በላይ፤ መንግሥት ሰላምን ለማስፈንና የዜጎችን ችግር ለመፍታት የሚያስችሉ ሥራዎች ላይ አተኩሮ መሥራት አለበት ባይ ናቸው፡፡

በሾላ ገበያ ሲገበያዩ ያገኘናቸው ወይዘሮ ማርታ አለማየሁ የአትክልት ገበያው ውድ የሚባል ነው ይላሉ፡፡ ሽንኩርት በ130 ብር፣ ድንች በ28 ብር፣ ቀይ ስር በኪሎ 50 ብር መሸመታቸውን ገልጸው፤ የሽንኩርት ዋጋ ከዓመት በዓሉ ጨምሮ መመልከታቸው ይገልጻሉ፡፡ ለአዲስ ዓመት ጥራት ያለው ቀይ ሽንኩርት 120 ገዝቼ ነበር ያሉት ወይዘሮዋ፣ 15 ቀን ባልሞላ ጊዜ የ10 ብር ጭማሪ መታዘባቸውን ነው የሚናገሩት፡፡

ከበዓል በኋላ ጭማሪ የታየው ሽንኩርት ላይ ብቻ ሳይሆን ሁሉም ምርቶች ላይ ነው የሚሉት ወይዘሮ ማርታ፤ ቲማቲም በኪሎ 90 ብር እንዲሁም ጥቁር ጎመን ከዚህ ቀደም በመደብ 20 ብር ይሸጥ የነበረው 30 ብር በመሆኑ ሳይገዙ መቅረታቸውን ይናገራሉ፡፡

በሾላ ገበያ የአትክልት ምርት በመሸጥ ላይ ያገኘናቸው ወይዘሮ ሱአድ አብዱል በበኩላቸው፤ ሽንኩርት ከ120 ብር እስከ 135 ብር፣ ቲማቲም 90 ብር፣ ድንች 28 ብር፣ ቀይስር 50 ብር፣ ካሮት 75 ብር፣ ነጭ ሽንኩርት 350 ብር እየሸጥኩ ነው ይላሉ፡፡

ሽንኩርትም ሆነ ሌሎች የአትክልት ምርቶች ላይ የተወሰነ የዋጋ ጭማሪ መኖሩን ያነሱ ሲሆን፤ ለዚህ ደሞ ምክንያቱ ከሚያመጡበት ቦታ የምርቶቹ ዋጋ መጨመሩ እንዲሁም የትራንስፖርትና መሰል ወጪዎች መደማመር መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

ወይዘሮ ሱአድ፤ ምርቶቹን የሚረከቡት በከተማዋ ካለ የአትክልት ተራ መሆኑን እና የዋጋ መወደድ እንጂ በማንኛውም ምርት ላይ እጥረት አለመኖሩን ጠቁመው፤ ችግሮቹን መፍታት ከተቻለ ዋጋው ቅናሽ ሊያሳይ እንደሚችል ያመላክታሉ፡፡

ኢፕድ ባደረገው ምልከታ በሰንበትና በመደበኛ ገበያዎች መካከል የዋጋ ልዩነቶች እንደሚስተዋሉ መገንዘብ ተችሏል፡፡ በዚህም ከቋሚ ገበያዎች አንፃር የጥራት ሁኔታው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ ኪሎ ቀይ ሽንኩርት ላይ እስከ 40 ብር፣ በቲማትም እስከ 20 ብር፣ በነጭ ሽንኩርት እስከ 80 ብር የሚደርስ የዋጋ ልዩነት ይስተዋላል፡፡

# የነጻ ገበያ ሥርዓቱ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ያሉ ርምጃዎች እና እንቅስቃሴዎች የሚደገፉ መሆናቸውን ይጠቁማሉ፡፡

የነጻ ገበያ ሥርዓትን ተከትለው የፖሊሲ ዝግጅቶች፣ የሕግ ማዕቀፎች፣ በዘርፉ ላይ ተዋናይ የሆኑ ተቋማት እና ባለሙያዎች ውሳኔዎቹን የመቀበል እና የማስፈጸም አቅማቸው በዛው ልክ ማደግ እንዳለበትም ያሳስባሉ፡፡

የፍትህ ተቋማቱን በምሳሌነት በማንሳት፤ የነጻ ገበያ ሥርዓት የበለጠ ወደ ተግባር እንዲለወጥና እንዲስፋፉ ፍርድ ቤቶች እንዲሁም የግልግል ማዕከላት መጠናከር፣ መስፋፋት እና አዳዲስ እንዲፈጠሩ መደረግ ይኖርበታል ባይ ናቸው፡፡

ፍርድ ቤቶች በንግድ ዙሪያ የሚመጡላቸውን ጉዳዮች የመዳኘት የንድፈ ሃሳብና የተግባር አቅማቸው የዳበረ ሊሆን ይገባል፡፡ በሂደቱም ፍርድ ቤቶች በቂ ዝግጅት ሊያደርጉ ይገባል ነው የሕግ አማካሪ አቶ ወይናለም የሚሉት፡፡

የግልግል እና የማስማማት ማዕከላት ገላጋይ ብለው የዘረዘሯቸው ባለሙያዎቻቸውን የማብቃት ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡ የሕግ ቢሮዎች፣ ጠበቆችና የሕግ አማካሪዎች ከጊዜው ጋር ተራማጅ የሆነ እውቀትን ሰንቀው መዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል ሲሉም ያክላሉ፡፡

ጠበቃና የሕግ አማካሪ ሚካኤል የወጡ ሕጎችን ባግባቡ ማስፈጸም የሚችሉ ተቋማት መኖር እንዳለባቸው በመጠቆም፤ ለተግባሩ ትኩረት ተሰጥቶት መሠራት አለበት፣ ስለተባለው ጉዳይ የሚገነዘቡና ወደ ተግባር መለወጥ የሚችሉ ብቁ ባለሙያዎችም መኖር አለባቸው ይላሉ፡፡

አያይዘውም፤ ኢንቨስተሮች በአንድ ሀገር ውስጥ ሥራ ለመጀመር ሲያስቡ ቀድመው የሚያናግሩት የሕግ ባለሙያዎችን ነው፡፡ በመሆኑም የሕግ ባለሙያዎች ራሳቸውን ሊያበቁ ይገባቸዋል፡፡ ፍርድ ቤቶች አካባቢም ቀደም ብሎ ሊሠራ የሚገባ ተግባር አለ፡፡ ችግር ሲፈጠር መብት የማስከበሪያ ሕጉን የሚተረጉሙት ዳኞች በመሆናቸው ቀድመው ሕጎቹን ማወቅ አለባቸው ነው የሚሉት፡፡

ዳኞች ከተጻፈው አልፎም ዓለም አቀፍ ግንዛቤ ያላቸው ቢሆኑ ይመረጣል የሚሉት ጠበቃና የሕግ አማካሪው፤ ነጻ ገበያን ብሔራዊ ባንክ ብቻ፣ ወይንም ንግድ ሚኒስቴር፣ ገቢዎች ሚኒስቴር እና ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በተናጥል የሚወጡት አይደለም፡፡ እያንዳንዳቸው የየራሳቸው አስተዋጽኦ እና ሚና ያላቸው በመሆኑ በቅንጅት ተናበበው መሥራት አለባቸው ባይ ናቸው፡፡

ኢትዮጵያ ዓለም አቀፉን የንግድ ድርጅት (WTO) እንድትቀላቀል አጋዥ የሕግ ማዕቀፎች ዝግጅት አስፈላጊ መሆኑን የሚገልጹት አቶ ወይናለም፤ የአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና ፈራሚ ሀገር እንደመሆኗ የባንክ ዘርፉ ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት ሲሆን የግድ የበቃ ተቋምና ባለሙያዎችን ማዘጋጀት ይገባል ነው የሚሉት፡፡ የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣንም የተዘጋጀ አስተሳሰብ አደራጅቶ መገኘት እንደሚጠበቅበት ይጠቁማሉ፡፡

መንግሥት የፖሊሲ ለውጦችን አድርጓል፡፡ ይህንን ተከትሎም የተለያዩ ሕጎች ወጥተዋል፡፡ የግልግል ማዕከልን በምሳሌነት ብንወስድ ራሱን የቻለ የግልግል አሠራር አዋጅ ያለው አካሄድን የሚደነግግ ዝርዝር ሕግ ወጥቶለታል፡፡ ይህ ይበል የሚያሰኝ ነው ይላሉ አቶ ወይናለም ፡፡

የአክሲዮን ሽያጭም እየመጣ ነው፡፡ ይህም ራሱን የቻለ የውጭ ሀገር ባለሀብቶችን የሚስብ እንደሚሆን ስለሚገመት በጋራ እስካልሠሩ ድረስ ስኬታማ መሆን አይቻልም፡፡

የባለሙያዎች ዝግጅት በበቂ ሁኔታ የማይኖር ከሆነ ሂደቱ ላይ ተጽእኖ ሊፈጥር ይችላል፡፡ ስለጉዳዩ በብዙሃን መገናኛም ሆነ በሌሎች መንገዶች በአጀንዳነት ተይዞ ቀጣይነት እና ተከታታይነት ባለው መንገድ በስፋት ውይይት ሊደረግበት ይገባል ሲሉም ያሳስባሉ፡፡

አቶ ሚካኤል እንደሚናገሩት፤ የባለሙያዎችም ሆነ የሕዝቡ ግንዛቤ እንዲሰፋ መደረግ አለበት፡፡ ዓለም ላይ እየተፈጠሩ ያሉ ነገሮች በደንብ መታወቅ አለባቸው፡፡ ለዚህም ባለሙያዎችን ለማብቃት የተለያዩ ሥልጠናዎች መዘጋጀት አለባቸው፡፡

ኢትዮጵያ የኒውዮርክ ስምምነትን መቀበሏ የውጭ ባለሀብቶች በኢትዮጵያ ላይ ያላቸውን እምነት ከፍ የሚያደርግ፣ ቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትመንቱንም በመጨመር መልካም አጋጣሚን የሚያሰፋ መሆኑን አቶ ወይናለም ያነሳሉ፡፡

እነዚህ እና ሌሎች በርካታ አዳዲስ የሕግ ማእቀፎችን ለማውጣት በመንግሥት የተወሰዱ ርምጃዎች ይበል ያሰኛሉ፡፡ ነገር ግን የሕጎቹ መውጣት ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ የተቋማቱ መጠናከር፣ የግለሰቦቹ ዝግጅትም ይጠበቃል ነው የሚሉት፡፡

ከነጻ ገበያው ጋር ተያይዞ እየተወሰዱ ያሉ ርምጃዎች ለማህበረሰቡ፣ ለሕግ አውጭው፣ ለጠበቃው፣ ለመንግሥት፣ ለፖሊሲ አውጭውም ሆነ ለንግዱ አካላት አዲስ ሃሳብ ናቸው፡፡ ስለዚህም የሚጠበቀውና ትግበራው ሊለያይ፣ ያልታሰቡና ያልተዳሰሱ ነገሮች ሊከሰቱ የሚችሉበት ዕድል ሊኖር ይችላል ሲሉም ያስጠነቅቃሉ፡፡

ሌሎችም ስጋቶች እንደሚኖሩ ጠብቆ በደንብ መዘጋጀት ያስፈልጋል የሚሉት አቶ ወይናለም፤ የሕግ ክፍተት ካጋጠመም ለማረምና ለማስተካከል የሚያስችል ርምጃዎችን ለማድረግ መዘጋጀት እንደሚያስፈልግ ይገልጻሉ፡፡

ከማስፈጸምና ከመፈጸም አቅም ጋር የሚያያዝ የግለሰቦችና የተቋማት አቅምን እየገነቡ መቀጠል ተገቢ እንደሆነ እና ቀድመው የተገበሩ ሀገራትን ልምድና ተሞክሮ መቅሰምም እንደሚያስፈልግም ይጠቁማሉ፡፡

አቶ ሚካኤል ሌሎች ሀገራት በኢትዮጵያ እንደተደረገው አይነት የፖሊሲ ለውጥ ሲያደርጉ በብዙኃን መገናኛ ሕዝቡ እንዲያውቀው ተደርጎ፣ የመንግሥት የፖሊሲ ውሳኔ የእያንዳንዱ ሰው ሕይወት ላይ ምን ሊያደርግ እንደሚችል ውይይት እንደሚደረግ ይጠቅሳሉ፡፡

በመሆኑም ተሞክሮውን በመቀመር በቂ የግንዛቤ ፈጠራ መሠራት ይኖርበታል፡፡ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው ሰዎች ይበልጥ ተሳታፊ እንደሚሆኑ ታሳቢ በማድረግ የውይይት መድረኮችን ማዘጋጀት ይጠበቃል ነው የሚሉት፡፡

በጉዳዩ በቂ እውቀት እና የውጭ ቋንቋዎች እውቀት ያላቸው ኢትዮጵያውያንን በመጠቀም ጉዳዩን በደንብ ማዳበር እንደሚገባ ነው የሚመክሩት፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት ኢኮኖሚውን ለማሳደግ የነጻ ገበያ ሕግጋትን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንደሚያደርግ ይፋ ያደረገው መስከረም 28 ቀን 2011 ዓ.ም የሁለቱ ምክር ቤቶች መክፈቻ ላይ እንደነበር ይታወሳል፡፡

# ከቴክኒክና ሙያ ፊት የተደቀኑ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በቴክኒክ እና ሙያ ሥልጠና ኢንስቲትዩት የጥናት እና ምርምር ዳይሬክተር አቶ አንማው ታደሰ እንደሚናገሩት፤ አብዛኛው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎቻቸውን የሚያዘጋጁት ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለማስገባት ብቻ ነው። ነገር ግን በተግባር ሲታይ ከየትምህርት ቤቶቹ ውስን ተማሪዎች ብቻ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ይገባሉ። ከሰማንያ በመቶ በላይ ተማሪዎች ወደ ቴክኒክና ሙያ የሚያስገባውን ውጤት ይዘው ይቀመጣሉ።

ወደ ዘርፉ የሚገቡ ተማሪዎች በትምህርት የወደቁ ናቸው የሚል የተሳሳተ ግንዛቤ በመኖሩ ተማሪዎች ወደ ቴክኒክና ሙያ ተቋማት እንዳይመጡ አንዱ ምክንያት መሆኑን ያመለክታሉ።

የግል ቴክኒክ እና ሙያ ተቋማት የአሠራር ክፍተት ያለባቸው በመሆኑ ሠልጣኞች በአጭር ጊዜ ውስጥ ሥልጠና ጨርሰው እንዲወጡ እንደሚደረጉ ያስረዳሉ። ይህ ከጥራትና ከብቃት አንፃር አጠያያቂ ነው፤ ሠልጣኞችም በግል ተቋማት የሚገቡ ቁጥራቸው ከፍተኛ ሲሆን ወደ መንግሥት ተቋማት የሚገቡት ግን ቁጥራቸው አነስተኛ መሆኑን ይጠቁማሉ።

በፊት ከአስረኛ ክፍል ወደ ዘርፉ የሚገቡ ተማሪዎች እንደነበሩ በመጥቀስ፤ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አስራ ሁለተኛ ክፍል ጨርሰው ወደ ዘርፉ የሚገቡ ተማሪዎች በተደረገ ጥናት ቁጥራቸው እየቀነሰ መምጣቱን ይጠቅሳሉ። ለዚህም ምክንያቱ ዘርፉ የወደቁ ተማሪዎች የሚገቡበት ነው የሚል የግንዛቤ ችግር በመኖሩ መሆኑን ይናገራሉ።

የመንግሥት ቴክኒክና ሙያ ተቋማት የአቅም ውስንነት እንዳለ እና ሠልጣኝ ተማሪዎች ሲገቡ ከተግባር ጋር የተያያዘ ስለሚሆን አስፈላጊው ግብዓት ያልተሟላላቸው ተቋማት መኖራቸውን በመግለፅ፤ በርካታ ተማሪዎች አቋርጠው እንዲሄዱ ማድረጉን ያብራራሉ። በዚህም ምክንያት የዘርፉ ተማሪዎች ቁጥር ዝቅተኛ መሆኑን ይጠቅሳሉ።

እንደ አቶ አንማው ገለፃ፤ ቴክኒክ እና ሙያ ትምህርት ሥልጠና በሀገራችን ትልቅ ኢኮኖሚው ላይ ለውጥ ያመጣል ተብሎ ፖሊሲ ወጥቶለታል። ሥራው ወደ ተግባር ሲገባ ችግሮች በመኖራቸው ወደ ዘርፉ የሚገቡ ተማሪዎች ቁጥር አናሳ በመሆኑ ኢኮኖሚው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ፈጥሯል።

አቶ ሀብታሙ ሙሉጌታ በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ኢንስቲትዩት የሪሰርች እና ማህበራዊ አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ናቸው። እንደ እሳቸው አባባል፤ አሁን ባለው ሁኔታ ወደ ዘርፉ የሚቀላቀሉ ሠልጣኞች ከ12ኛ ክፍል ፈተና ተፈትነው ውጤት ያልመጣላቸው ናቸው። ነገር ግን ዘርፉ በሀገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት ላይ ከፍተኛ ሃይል ያለው በመሆኑ ፍላጎት ላይ መሠረት ባደረገ መልኩ ሊሰጥ ይገባ ነበር።

ለዘርፉ እንደ ዋነኛ ችግር የሆነው የአመለካከት ችግር መሆኑን የሚጠቅሱት አቶ ሀብታሙ፤ ለአብነትም የዕደ ጥበብን ሙያ ለሀገር ዕድገት መሠረት መሆኑን ከመረዳት ይልቅ ዝቅ አድርጎ እና አንቋሾ የማየት ባህሎች ከድሮ ጀምረው ሲንከባለሉ የመጡ ችግሮች መሆናቸውን ያስታውሳሉ።

በመሆኑም ይህ የቆየ አመለካከት የቴክኒክና ሙያ የሚገቡ ሰዎች ክህሎት ያላቸው እና ለሀገር ዕድገት የሚበጁ የፈጠራ ሥራዎችን መሥራት የሚችሉ ውጤት ያላቸው ተማሪዎች ወደ ዘርፉ መግባት እየቻሉ ውጤታቸው ዝቅተኛ የሆኑትን እና የመጨረሻ አማራጭ ተደርጎ በመታየቱ ማህበረሰቡ ላይ ትልቅ ችግር ሆኖ መቆየቱን ይናገራሉ።

አብዛኞቹ ወጣቶች የማህበረሰብ እና የጓደኞቻቸው ተፅእኖ ስር ስለሚወድቁ በራሳቸው የመወሰን እና የተሰጣቸው ክህሎት ለመጠቀም እንደሚገደቡ ይጠቅሳሉ። ሌላው የዘርፉ ችግር ከታች ጀምሮ በክህሎት እየኮተኮቱ የማሳደግ ባህል ተዳክሞ መቆየቱ ሠልጣኞቹ የመጀመሪያ ምርጫቸው ዩኒቨርሲቲ መግባት ሲሆን ወላጆችም እንደ ስኬት የሚያዩት ይህንኑ መሆኑ ለቴክኒክና ሙያ የሚሰጠው ግምት አናሳ እንዲሆን ማድረጉን ያመለክታሉ።

ለዓመታት የተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች እንዲስፋፉ ተደርገው በርካታ ተማሪዎች ቢመረቁም ሥራ የማግኘት እድላቸው ዝቅተኛ እየሆነ መምጣቱን ያስረዳሉ። በዚህም ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ላይ የሚስተዋለው ኋላ ቀር አመለካከት በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጫና እየፈጠረ እንደሚገኝ እየተስተዋለ መሆኑን ይገልፃሉ።

እንደ አቶ ሀብታሙ አባባል፤ የቴክኒክ እና ሙያ ተቋማት ከዚህ ቀደም የነበራቸው ልምድ ተማሪዎች በብዛት አስገብተው በብዛት የማስመረቅ ሁኔታ ነበር። የትምህርት ፕሮግራሞች ሲከፈቱ አካባቢያዊ እና ቀጣናዊ ገበያን ያላገናዘቡ በመሆናቸው ገበያ እና ሥራ በቀላሉ አይገኝላቸውም። በዚህም በጥራት አስተምሮ የማስመረቅ ሁኔታ አልነበረም።

በቅርቡ በሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር በተደረገው የሪፎርም ሥራ መሠረት በማድረግ በስምንት ዞኖች በመክፈል በግብርና፣ ኢንዱስትሪ፣ መዓድን እና ሌሎች ካላቸው ፀጋ አንፃር በየትኛው ዘርፍ ማሠልጠን እንዳለባቸው በመገንዘብ በተወሰኑ ፕሮግራሞች ላይ ወጣቶች እንዲሠሩ እየተደረገ መሆኑን ያመለክታሉ።

በሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር በኩል ወጣቶች የእጅ ሙያተኞች ሆነው የተግባር ልምምድ ወስደው ለራሳቸው ሥራ ፈጥረው ለሌሎችም ለመትረፍ እንዲችሉ ከፍተኛ ሁኔታ እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ የሙያ ልምምዱ ከአካዳሚ ዕውቀት ጋር አብሮ እንዲመጣ በማድረግ በግለሰቡ ፍላጎት መሠረት የተሠራ ሪፎርም በመተግበር ውጤታማ ማድረግ እንደሚቻል ይገልፃሉ።

በዘርፉ የሚሰማሩ ሠልጣኞች እንዲበራከቱ ዘርፈ ብዙ ሥራዎች ያስፈልጋሉ፤በተለይ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ሀብት አደርጅተው ወጣቱ ዕውቀትን ወደ ገንዘብ መለወጥ የሚችልበትን አሠራር ውስጥ መግባት አለባቸው ይላሉ።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## በሀገር ውስጥ የተሰራው የተለያዩ የእህል ዓይነቶችን የሚወቃው ማሽን

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ከተለያዩ የሀገሪቷ አካባቢዎች የመጡ ስምንት የቴክኒክና ሙያ አሰልጣኞች አንድ ወቅት ላይ በአንድ ጉዳይ ዙሪያ ተገናኝተው እንዲመክሩ ተደረገ። እንዲህ በአንድ ላይ መሰብሰባቸው ትልቅ አላማን ያነገበም ነበር። አሰልጣኞቹ የተገናኙበትን አላማ ከግብ ለማድረስ መክረውና ዘክረው፤ አውጥተውና አውርደው በአንድ ሃሳብ ይስማማሉ። ይህም ከየመጡበት አካባቢ አሉ ያሏቸውን የአርሶ አደሩን ችግሮች ነቀሰው በማውጣት ዋንኛ በሚሉት ላይ ትኩረት አድርገው በመምከር መፍትሔ ማስቀመጥ ነው።

ችግር ናቸው ብለው ካሰቧቸው መካከል ዋንኛው አርሶ አደሩ በእጅጉ የደከመበት የእህል አዝመራ በምርት መሰብሰብ ሂደት የሚያጋጥመው የምርት ብክነት አንዱ ሆነ። አሰልጣኞቹ ለእዚህም መፍትሔ ይሆናል ያሉት የእህል መውቂያ ማሽን መሥራት ሆኖ አገኙት፤ ይህን ሃሳባቸውን መሬት ለማውረድም እውቀታቸውንና ክህሎታቸውን አንድ ላይ ማድረጉን ተያያዙት፤ እንዳሰቡትም ምርትን ከብክለት የሚታደግ የእህል መውቂያ ማሽን መሥራት ቻሉ።

አሰልጣኝ ቃልኪዳን ሶዴ እና ሰባቱ የሙያ አጋሮቿ ናቸው ለእዚህ አላማ እንዲሰባሰቡ የተደረጉት። እነዚህ አሰልጣኞች በዚህ ታላቅ ሥራ ላይ እንዲሰማሩ እነሱን በማሰባሰብ ምቹ ሁኔታ የፈጠረው ደግሞ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ነው። አሰልጣኞቹ ለእዚህ አላማ እንዲሰባሰቡ ከመደረጋቸው በፊት በቴክኒክና ሙያ ተቋማት ሆነው የየራሳቸውን የፈጠራ ሥራ የሰሩ ናቸው። የፈጠራ ሥራቸውን የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር በሚያዘጋጀው ብሩህ ተስፋ ውድድር ላይ ያቀረቡም ናቸው።

በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር እነዚህ በተለያዩ ቦታዎች የተጀመሩት የፈጠራ ሥራዎች በጋራ ቢሰሩ ድምር ውጤታቸው የተሻለ መሥራት ያስችላል በሚል ስለታመነበት አሰልጣኞቹ በክረምት መርሃ ግብር በአንድነት መሰብሰባቸውን አሰልጣኝ ቃልኪዳን ትናገራለች። አሰልጣኞቹ የአርሶ አደሩን ችግር በቅርበት እንደሚያወቁ ታምኖበትም፤ ዋንኛ ችግር ነው ብለው ያሰቡትን የእህል መውቂያ ማሽን እንዲሰሩ መደረጉን ትገልጻለች።

አርሶ አደሩ እስካሁን እየተቸገረበት ያለው ጉዳይ ዋንኛው ምክንያት ጉልበቱን ሳይቆጥብ ለፍቶና ደክሞ፣ በበሬ አርሶ ያለማውን ሰብል ለመውቃት የሚጠቀመው ኋላቀር መንገድ መሆኑ ነው። ይህም ምርቱን በአግባቡ እንዳይሰበሰብ ሲያደርገው ኖሯል፤ ለብክነት የሚዳረግበትን ሁኔታም ይፈጥራል። ችግሩ ቢፈታ ምርትና ምርታማነትን መጨመር እንዲሁም አርሶ አደሩን ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል። እነሱም ለእዚህ ችግር የመፍትሔ ሃሳብ በማፍለቅ የእህል መውቂያ ማሽን መሥራታቸውን አሰልጣኟ አስታውቃለች።

ቃልኪዳን እንዳለችው፤ የእህል መውቂያ ማሽን ሃሳቡ ከመምጣቱ በፊት አሰልጣኞቹ በየግላቸው የበቆሎ፣ የጤፍና የሌሎች እህሎች መውቂያ ማሽኖችን ሰርተዋል። በእዚህ መነሻነትም ነው ሁሉንም የእህል ዓይነቶች መውቃት የሚችል ማሽን ለምን አንሰራም በሚል መነሻ ሃሳብ ወደ ሥራ የገቡት።

"ሁላችንም በየአካባቢያችን ያሉ ችግሮችን ለመፍታት በማሰብ የበቆሎ መፈልፈያ፣ የጤፍ መውቂያ እያለን የተለያዩ የእህል የመውቂያ ማሽኖችን ሰርተናል። እኔ በበኩሌ ሁሉንም የእህል ዓይነቶች የሚወቃ ማሽን ሰርቼ ነበር። ይሁን እንጂ ይህ ሁሉ የፈጠራ ሥራ አንድ ላይ ቢመጣ እንደ ሀገር ጥሩ ሥራ በመሥራት አንድ ማሽን ማውጣት እንደሚቻል ስለታመነበት በአንድነት ማሽኑን መሥራት ተችሏል» ስትል አብራርታለች።

አሰልጣኝ ቃልኪዳን እንደምትለው፤ አሁን ሁሉንም የእህል ዓይነቶች መውቃት የሚችል ማሽን ሰርቷል። ማሽኑ ጤፍ፣ ባቄላ፣ በቆሎ የመሳሰሉትን ማንኛውንም የእህል ዓይነቶች መውቃት ይችላል። ማሽኑ ብረት በማቅለጥ፣ በመበየድና የመሳሰሉትን በመሥራት ሀገር ውስጥ ከሚገኙ ጥራታቸውን ከጠበቁ ሀገር ውስጥ ከሚገኙ ብረታ ብረቶች የተሰራ ሲሆን፣ እንደ ቺንጋና ዲናሞ ያሉ እቃዎች ብቻ ከውጭ የመጡ ናቸው።

በተመሳሳይ የተለያዩ የእህል ዓይነቶችን የሚወቃ ማሽን ከውጭ ሀገር ይመጣል፤ ይህ ማሽን በሀገር ውስጥ ከተመረተው ጋር ሲነጻጸር ሰፊ ልዩነት አለው። ከውጭ የሚገባው ማሽን እንደ በቆሎና ባቄላ ያሉ ጥራጥሬዎችን ለመውቃት ይቸግራል። ምክንያቱ በውስጡ ያለው መውቂያ ጤፍ፣ ስንዴ ፣ ሩዝ ፣ ገብስ እና ሌሎች የእህል ዓይነቶችን ለመውቃት ብቻ ተብሎ የተዘጋጀ ነው። በሀገር ውስጥ የተሰራው አዲሱ ማሽን ግን ሁሉንም የእህል ዓይነቶች ያለምንም ችግር መውቃት እንዲችል ተደርጎ የተሰራ ነው።

ማሽኑ የተለያዩ የእህል ዓይነቶች እንዲወቃ ካስፈለገ እንደየእህሉ ዓይነት ሊያገለግሉ የሚችሉ የተለያዩ መቀያየሪያዎች መሳሪያዎች ተዘጋጅተውለታል። መሳሪያዎቹ በቀላሉ እየተፈቱ ሊቀየሩ የሚችሉ ናቸው። መሳሪያዎቹን መቀየር የሚያስፈልገው የአገዳ እህል የሚባሉት በቆሎና ባቄላን ለመውቃት ሲፈለግ ብቻ ነው። ሌሎች 14 ዓይነቶች መሳሪያዎችን ግን ምንም ዓይነት መቀየር ሳያስፈልግ እንዳለ መጠቀም ይቻላል።

ማሽኑ እህሉን ወቅቶ፣ አነፍሶና አበጥሮ ምርቱን ወደ ተገጠመለት ታንከር እንዲገባ ያደርጋል፤ ምርቱ 50 ኪሎ ግራም ሲሞላ ንጽህ የሆነው ምርት ወደ ማዳበሪያ ይገለበጣል። ገለባውና ሌሎች ተረፈ ምርቶችን ደግሞ ለከብቶች መኖ በሚሆን መልኩ አዘጋጅቶና አስተካክሎ ያወጣል።

አሰልጣኝ ቃልኪዳን፤ ማሽኑ አሁን ላይ በሰዓት 18 ኩንታል እህል መውቃት ያስችላል ስትል ጠቁማ፣ ማሽኑን ከዚህ ባነሰ መጠን የሚፈልጉ አርሶ አደሮች ካሉ እንደየአርሶ አደሩ ፍላጎት በሰዓት እስከ 10 ኩንታል እህል እንዲወቃ አድርጎ መሥራት ይቻላል ብላለች።


እሷ እንዳለችው፤ ይህን ማሽን በ250 ሺ ብር ለመሸጥ ታስቧል። ከውጭ የሚመጣው ግን በጣም ውድ እና በግማሽ ያህል ልዩነት ያለው ነው። ማሽኑ የሚጠቀመው የኃይል ዓይነትም እንደ ደንበኛው ፍላጎት የሚወሰን ይሆናል። የኤሌክትሪክ ኃይል ተደራሽ በሆነበት አካባቢ በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሰራ ሲሆን፤ የኤሌክትሪክ ኃይል ተደራሽ ባለሆነባቸው አካባቢዎች ደግሞ በነዳጅና በሶላር እንዲሰራ አድርጎ መሥራት ይችላል።

ማሽኑ በአንድ ጊዜ ተሰርቶ አሁን ያለውን መልክ የያዘ ሳይሆን፣ በየጊዜው በተሰጡት አስተያየቶች መሰረት ክፍተቶችን በመሙላት ጥራቱ የተጠበቀ እንዲሆን ተደርጎ የተሰራ ነው ብላለች። የማሽኑ የጥራት ደረጃም በኢትዮጵያ ጥራትና ደረጃዎች ኤጀንሲ የተረጋገጠ መሆኑን ገልጻለች።

በአሁኑ ወቅት ኬር ይሁን ፋርሚንግ ቴክኖሎጂ የተሰኘ ድርጅት በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወርክሾፕ በመክፈት ማሽኑን ለማምረት በሂደት ላይ እንደሆነም ጠቁማለች። ለዚህም በኢትዮጵያ ልማት ባንክ የመሥሪያ ቦታና እና የተለያዩ ማሽነሪዎች ድጋፍ እየተደረገላቸው መሆኑን ገልጻለች።

ይህ ማሽን ባለፈው ዓመት በሳይንስ ሙዚየም በተዘጋጀው የፈጠራ ውድድር ላይ ቀርቦ ሁለተኛ ወጥቷል የምትለው ቃልኪዳን፤ ከአዕምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት የፈጠራ ባለቤትነት ማረጋገጫ ለማግኘት በሂደት እንደሚገኝም ታስረዳለች። ቀደም ሲል በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የሚደገፉ የፈጠራ ሥራዎች በአውደ ርዕይ ቀርበው በቀረቡበት ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ይህን የፈጠራ ሥራ እንደጎበኙትና ማበረታቻም እንደሰጧቸው አስታውቃለች። በወቅቱም ማሽኑ ከተመረጡ የፈጠራ ሥራዎች አንዱ ሆኖ መጠቀሱን አስታውሳ፣ በመንግሥት በኩል ማሽኑን እንደሀገር ለሁሉም ክልሎች ለማዳረስ እቅድ ተይዞ እየተሰራ መቆየቱንም ገልጻለች።

በዚህም ቅድሚያ የተሰጠው ለኦሮሚያ ክልል መሆኑን ጠቅሳ፣ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት አማካኝነት 100 ያህል ማሽኖች እንዲመረቱ ጥያቄ መቅረቡን ትጠቁማለች። ማሽኑን ለማምረት በቅድሚያ የንግድ ፈቃድ ማውጣት እንደሚያስፈልግና እሱም ሂደት ላይ



**በሀገር ውስጥ የተሰራው አዲሱ ማሽን ግን ሁሉንም የእህል ዓይነቶች ያለምንም ችግር መውቃት እንዲችል ተደርጎ የተሰራ ነው**

መሆኑን ጠቅሳ፣ የንግድ ፈቃድ ጋር ተያይዞ ያለው ሂደት ገና ያልተጠናቀቀ በመሆኑ እስከዚያው ድረስ ከሌላ የቴክኖሎጂ ድርጅት ጋር በመሆን በፍጥነት ወደ ማምረት ሥራው ለመግባት እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው ብላለች።

እሷ እንዳለችው፤ ማሽኑ ከተመረተ በኋላ ክልሉ ለአርሶ አደሩ ተደራሽ የሚያደርገው ይሆናል። ሥራው የመጀመሪያ እንደመሆኑ መጠን የኦሮሚያ ክልል ማሽኑ እንዲሰራ ያዘዘ ቢሆንም፣ ሌሎች ክልሎችም እንዲሁ ማሽኑ እንዲመረትላቸው የሚፈልጉ ከሆነ ድርጅቱን በመጠየቅ እንደ ቅደመ ተከተላቸው የሚስተናገዱ መሆኑን አስታውቃለች። «ማሽኑ ኤግዚቢሽን ላይ በቀረበበት ወቅት ያዩ እንዲሰራላቸው የሚፈልጉ ግለሰቦችና ድርጅቶችም ከእኛ ጋር እየተነጋገሩ ነው» ትላለች።

እንደ አሰልጣኟ ማብራሪያ፤ ማሽኑን የተለያዩ የሚዲያ አማራጮችን በመጠቀም እንዲተዋወቅ እየተደረገ ነው። የማምረቱ ሥራ በደንብ ሲጀመር የማስተዋወቁ ሥራም እንዲሁ ተጠናክሮ ይቀጥላል። በዚህም አርሶ አደሩ ስለማሽኑ አውቆ እንዲገዛና እንዲጠቀምበት ይደረጋል።

በቀጣይም በህብረተሰቡ ዘንድ ያሉ ችግሮችን በደንብ በመመልከት ለእነዚህ መፍትሔ ሊሆኑ የሚችሉ የፈጠራ ሥራዎች እንደሚሰሩም ጠቁማለች። በዚህም መሠረት በእቅድ የተያዙ ሥራዎች እንዳሉም ገልጻ፣ ከእነዚያም ውስጥ አንድ በበሬ ማረስ ሊያስቀም የሚችል በራሱ የሚያርስ፣ የሚያጨድ እና ምርቱን የሚሰበስብ እንደ ሞተር ባይስክል ተንቀሳቃሽ የሆነ ማረሻ ለመሥራት መታቀዱንም ጠቁማለች።

የመውቂያ ማሽኑ ከውጭ ከሚገባው ማሽን ጥራት ያለው መሆኑን አመልከታ፣ ማሽኑን ወደፊት በሰፊው በማምረት ከውጭ የሚመጣውን በማስቀረት እና የሀገር ውስጥ ፍላጎትን በማሟላት ብቻ ሳይወሰን ማሽኑን ወደ ውጭ ሀገራት ለመላክ መታቀዱንም ተናግራለች።

ድርጅቱ ወደ ማምረት ሥራው ሲገባ ከመጀመሪያ ገና ለ15 ያህል ሥራ አጥ ዜጎች የሥራ እድል ይፈጥራል የምትለው ቃልኪዳን፤ ምርቱ እየጨመረና እየሰፋ ሲሄድ ትልቅ ድርጅት እንደሚሆንና ለብዙ ዜጎች የሥራ እድል እንደሚፈጥርም ተናግራለች። በአምስት ዓመታት ውስጥ ከሁለት ሺ ለሚልቁ ዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር እንደሚያስችል ታስረዳለች።

እንደ አሰልጣኟ ማብራሪያ፤ ማሽኑን እውን ያደረጉት ስምንቱ አሰልጣኞች በተለያዩ የትምህርት ዘርፍ የተመረቁ ሲሆን፣ ማሽኑን ለመሥራት ሁሉም ያለውን እውቀት አውጥቷል። ድርጅቱ ማሽኑን የሚበይድ፣ ዲዛይን የሚያወጣ፣ ኤሌክትሪክ ሲስተሙን የሚሰራ፣ በሁሉም ሙያ ዘርፍ ያሉ ባለሙያዎች የተካተቱበት ነው።

«ይህ እድል መፈጠሩ በራሱ ትልቅ ሥራ እንድንሰራ አድርጎናል። ይህንን የፈጠራ ሥራ ለመሥራት በአንድ መሰብሰባችን ውጤታማ የሆነ ሥራ እንድንሰራ አስችሎናል። » ያለችው አሰልጣኝ ቃል ኪዳን፣ «አንዱ ያለው እውቀት ሌላው ሊኖረው ስለማይችል ሁሉም ያለውን እውቀት እንዲህ አንድ ላይ አምጥቶ በጋራ መሥራቱ ማሽኑን ለመሥራት የሚያስችሉ ክህሎቶችን እንድናገኝ አድርጎናል። የእውቀት ሽግግር እንዲኖር፣ የሥራ መንፈሳችን እንዲታደስና ለቀጣይ ሥራ ተነሳሽነት እንዲኖረን አድርጓል» ስትል አብራርታለች።

በአሁኑ ወቅት እንደ ሀገር ብዙ ሃሳብ ያላቸው ወጣቶች እንዳሉም ጠቁማ፣ እነዚህ ሃሳቦች በአንድ ቢጣመሩ ሀገሪቱ ከውጭ ለማስገባት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የምታወጣባቸውን ምርቶች በሀገር ውስጥ ምርት መተካት እንደሚቻል የማሽኑ እውን መሆን እንደሚያሳይ ትገልጻለች።

ከውጭ የሚመጣውን የሚተካ ብቻ ሳይሆን እንዲያውም የበለጠ የተሻለ ሥራን መሥራት እንደሚቻልም ገልጻ፣ ‹ለዚህም እኛ በአንድነት ሆነን ይህንን ማሽን መሥራት መቻላችን ጥሩ ማሳያ ነው ብላለች። «እኛ ከውጭ የሚመጣውን የሚተካ ብቻ ሳይሆን የበለጠ ማሽን ነው የሰራነው። ምክንያቱም እኛ የሰራነው ምርቱን ወቅቶ፣ አነፍሶ፣ አበጥሮ እህሉን ብቻ የሚሰጥ ማሽን ነው» በማለትም ነው ያብራራችው።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ ትንታኔ

# የቱሪዝም ዘርፉ ፈተናዎች እና ተስፋዎች

ምሕረት ሞገስ

ባለፈው የፈረንጆቹ ዘመን በ2023 በዓለም በቱሪዝም ዘርፍ የላቀ አፈፃፀም በማግኘት እና በሰፊው በመጎብኘት ከፍተኛ ገቢ በማግኘት ታዋቂነትን ከተረፉ ሀገራት መካከል ቀዳሚዋ ፈረንሳይ ናት። ፈረንሳይን ተከትላ ስፔን በመቀጠል አሜሪካን፣ ቻይና፣ ጣሊያን፣ ቱርክ፣ ሜክሲኮ ፣ ታይላንድ እና ጀርመን ተጠቃሾች ናቸው። እነዚህ ሀገራት ምንም እንኳ ቀድሞም በቱሪዝም ዘርፍ ከፍተኛ ገቢን በማግኘት እና በመጎብኘት ታዋቂነትን ያተረፉ ቢሆኑም፤ በዓለም ላይ ተከስቶ የነበረው የኮረና ወረርሽኝን ተከትሎ የቱሪዝም ዘርፋቸው በእጅጉ ክፉኛ በመጎዳቱ ገቢያቸው ተቀዛቅዞ የጎብኚ ቁጥራቸውም ቀንሶ ነበር።


ባለፈው 2023 ግን ገቢያቸው ከኮረና በፊት ወደነበረበት ደረጃ መመለስ ችሏል። ፈረንሳይ፣ ስፔን እና አሜሪካን የመሳሰሉ ሀገራት፤ እያንዳንዳቸው 100 ሚሊየን የሚጠጉ ጎብኚዎችን ወደ ሀገራቸው በመሳብ እና እንዲጎበኙ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ከፍተኛ ገቢ ሲያገኙ ኢትዮጵያ ግን አንድ ሚሊየን ቱሪስት ለመሳብ ተቸግራለች። እነሳዊዲ አረቢያን የመሳሰሉ ሀገራት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በቱሪዝም ዘርፍ ላይ ከፍተኛ ሥራን በማከናወናቸው የተሻለ ገቢ ማግኘት እና የተሻለ ቁጥር ያለው ጎብኚን መሳብ ችለዋል። ኢትዮጵያ ግን በተባበሩት መንግሥታት የዓለም የቱሪዝም ድርጅት መረጃ እንደሚያመለክተው፤ በማክሮ ኢኮኖሚ ችግሮች ብትፈተንም የቱሪዝም ዘርፉን ለማሳደግ ትግሏን ቀጥላለች። እ.ኤ.አ. ከ 2022 የሰላም ስምምነት በኋላ በቱሪስቶች መጎብኘቷን ቀጥላለች። ነገር ግን ከሌሎች ሀገሮች ጋር ተፎካክራ የጎብኚዎችን ቁጥር በሚሊየን ማስቆጠር እና ከፍተኛ ገቢ ማግኘት አዳግቷታል።

ለምን የኢትዮጵያ የቱሪዝም ዕድገት በሚፈለገው መጠን መሆን አልቻለም ለሚለው ዘርፉን የሚመሩ ኃላፊዎች እና ባለሞያዎች የሚሉት አላቸው። የቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ግርማ እንደሚገልፁት፤ ለአንድ የቱሪዝም እንቅስቃሴ አስፈላጊ ከሆኑ ጉዳዮች መካከል ዋነኛዎቹ መሠረተ ልማቶች ናቸው። ለምሳሌ የትራንስፖርት ሁኔታው ላይ መንገድ፣ ቴክኖሎጂው ላይ የቴሌኮም አገልግሎቶች መሻሻል አለባቸው። ከእነዚህ በተጨማሪ የጤና አገልግሎት ላይ ብቁ የሰው ኃይል መኖር፣ የሠራተኞች አቅም፣ የሰላም እና የፀጥታ ጉዳይ፣ የፖሊሲ ጉዳዮች እና ሌሎችም በጣም አስፈላጊ የሆኑ የዘርፉን ተወዳዳሪነት የሚወስኑ ጉዳዮች አሉ።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለፃ፤ በኢትዮጵያም የኮረና ወረርሽኝ በቱሪዝም ዘርፉ ላይ ከባድ ጫና ፈጥሮ ማለፉ የሚዘነጋ አይደለም። ሌሎች ሀገሮች ከኮረና በፊት የነበራቸውን የቱሪዝም ዘርፍ ገቢ ማግኘት ችለዋል። በኢትዮጵያ በኩል ግን ከኮረና በኋላም የሰሜኑ ጦርነት ቀጥሎ የመጣ በመሆኑ እና በጦርነቱም ምክንያት ሰዎች በቀላሉ ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ በመገደቡ እንዲሁም የኤምባሲ ማስፈራሪያዎች እና ክልከላዎች ከፍተኛ ጫና በመፍጠራቸው ከኮረና በኋላም የቱሪዝም ዘርፉ ፈተና ቀጥሏል።

በሌላ በኩል የአገልግሎት ጥራት አሁንም ፈተና ውስጥ ነው። የአገልግሎት ጥራት እንዲሻሻል የሆቴሎችን ደረጃ መመደብ፤ ከዚህ በፊት የተመደቡትንም ዳግም ደረጃ መስጠት ያስፈልጋል። ሬስቶራንቶችን እና አስጎብኚ ድርጅቶችን እስከ አሁን ድረስ ጥራታቸውን መቆጣጠር እና ደረጃ መመደብ ላይ አልተደረሰም። አሁን መመሪያ በመፅደቁ ወደ ምደባ ይገባል። ስለዚህ መሠራት ካለበት አንፃር ብዙ መሥራት ይጠበቃል። ነገር ግን ኮረና እና የሰሜኑን ግጭት ተከትሎ የቱሪዝም ዘርፍ ላይ የሚደረሰውን ጉዳት ለመቀነስ በርካታ ኮንፈረንሶች ወደፊት እንዲመጡ በማድረግ ዘርፉን ለመደገፍ ጥረት ተደርጓል ብለዋል።

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የባሕል ጥናት እና የሥነ ጽሑፍ መምህሩ ዶክተር መስፍን ፈቃደ በሚኒስትር ዴኤታው ሃሳብ ይስማማሉ። በበኩላቸው ምንም እንኳ ኢትዮጵያ የቱሪዝም ዘርፉ ላይ ፈተናዎች ያሉባት ቢሆኑም፤ ብዙ ተስፋዎች እና ዕድሎች እንዳሏት ይናገራሉ። በተለይ ከወቅቱ ጋር በማያያዝ ከሚዳሰሱ ቅርሶች በተጨማሪ ለቱሪስቱ መስህብ ሊሆኑ የሚችሉ የሚከበሩ በዓላት መኖራቸውን በማስታወስ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከበዓላት



የሃላላ ኬላ ከፊል ገፅታ

አከባበር ጋር ተያይዞ ባሕሉን ይዞ የቆየ መሆኑ በራሱ ቱሪዝምን ለማሳደግ አመቺ መሆኑን ያብራራሉ። ይህንን ሲያስረዱ በኢትዮጵያ በተለያዩ ማህበረሰቦች ውስጥ የተለያዩ በዓላት አሉ። በበዓላቱ የሚለበሱት ልብሶችም ሆኑ ማጌጫዎቹ ሀገር በቀል መሆናቸው የቱሪዝም ዘርፉን ለማሳደግ በእጅጉ ይጠቅማሉ።

በነሐሴ እና በመስከረም ወር የሚከበሩ በዓላትን ተከትሎ ማህበረሰቡ የተለየ የፀጉር አሰራር፤ አልቦ እና ሌሎችም ማጌጫዎችን ይጠቀማል። ልብሱም የባሕል ነው። በዓላት ሲከበሩ ባሕሉን ጠብቆ መቆየቱ በቀጣይም ቱሪስትን ለመሳብ የሚያግዝ ትልቅ መሣሪያ ነው። ይህንን በመረዳት ወላጆች ለልጆቻቸው በዓላቸውን ከእነባህላቱ ማሳወቅ አለባቸው። ይህ በቀጣይም የኢትዮጵያ የቱሪዝም ዘርፍ አንደኛው ተስፋ ነው።

በሌላ በኩል ዶክተር መስፍን ዘርፉ እንዲያድግ እና ሀገር በቀል ሊጎበኝ የሚችሉ በዓላት እንዲያድጉ መንግሥታዊ የሆኑ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በስፋት መሥራት አለባቸው። በትምህርት ዘርፉም ላይ መካተት ይገባዋል። በዚህ ደረጃ መሥራት እና በዓላትን፣ ባሕሎችን እንዲሁም ቅርሶችን መጠበቅ ከተቻለ ወደፊት ኢትዮጵያ እንደሌሎቹ ሀገሮች ከቱሪዝም ዘርፍ ከፍተኛ ገቢ ማግኘት ትችላለች። ይህ በራሱ ትልቅ ተስፋ ነው ብለዋል።

የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት አሰልጣኙ አቶ ዐቢይ ንጉሴ በዶክተር መስፍን ሃሳብ ይስማማሉ። የቱሪዝም ዘርፍ ዕድገት ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዳለው በመጠቆም፤ ከውጪ ምንዛሪ ግኝት ባሻገር፣ ሰፊ የገንዘብ እንቅስቃሴ እንዲኖር በማስቻል፣ የሥራ ዕድል በመፍጠር እንዲሁም ማህበረሰቡ የሚታወቅበት ለምሳሌ ቡና፣ ማር እና ሌሎችም የማህበረሰብ ምርቶችን ለማስተዋወቅ ያስችላል የሚሉት አቶ ዐቢይ፤ በውጪ ገበያ እንዲኖራቸው እንደሚያግዝ ያመለክታሉ።

ወቅቱን ተከትሎ የአደባባይ በዓላት በስፋት መኖራቸውን በመጠቆም፤ በዓላቱ መኖራቸው በራሱ ሌሎች አካባቢዎች እንዲጎበኙ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራሉ። የሚሉት አሰልጣኙ፤ ለምሳሌ መስከረም በዓል ላይ የተሳተፉ ጎብኚዎች ስለበዓላቱ ለሌሎች ስለሚናገሩ ሀገርን ለማስተዋወቅ እና የቱሪዝም ዕድገትን ለማፋጠን ያመቻል ይላሉ። ክረምትን ተከትሎ በተለይ የገጠሪቱ አካባቢዎች መልከዓ ምድራቸው የሚያምር በመሆኑ፤ በተጨማሪ የፏፏቴዎቹም አቅም ስለሚጨምር ቱሪስቶች በተለይ በዚህ ወቅት የሚጎበኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት ቢቻል መልካም ነው። ይህ መኖሩን ማሰብ በተለይም በዓላቱ ብቻ ሳይሆኑ ኢትዮጵያ በክረምትም ጭምር ልትጎበኝ እንደምትችል ማሰብ እና በዛም ላይ መሥራት ከተቻለ ትልቅ ውጤት ማግኘት ይቻላል ይላሉ።

ሚኒስትር ዴኤታው በበኩላቸው፤ በርግጥም በዓላቱ በራሳቸው ለቱሪዝም ዘርፍ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው። ነገር ግን አሁን ላይ በስፋት እየተሠራ ያለው ሥራም የዘርፉ ትልቅ ተስፋ መሆናቸውን ያብራራሉ። ገበታ ለሸገር እና ገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶችን በመጥቀስ፤ በጣም ጥሩ ውጤት መጥቷል የሚል እምነት እንዳላቸው ያብራራሉ።

እንደ አቶ ስለሺ ገለፃ፤ ምንም እንኳ የሚቀሩ ብዙ ጉዳዮች ቢኖሩም አሁን ላይ ሊታዩ እና ሊገለፁ የሚችሉ ትልልቅ ለውጦች አሉ። በማለት ለምሳሌ ገበታ ለሸገርን ያነሳሉ። እንጦጦ፣ ወዳጅነት ፓርክ እና አንድነት ፓርክን ያየ ማንኛውም የቱሪዝም ዘርፍ ባለሞያ በቱሪስት መዳረሻነትም ሆነ የገንዘብ ምንጭ በመሆን ዘርፉ ትልቅ ተስፋ እንዳለው መገንዘብ አያዳግተውም ይላሉ።

እንጦጦም በስፋት እየተጎበኘ መሆኑን በማስታወስ፤ ብዙ ሰው የሚሳተፍበት ስፖርት እየተካሔደበት እንደሚገኝ እና በተለይ የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ዕድገት ትልቅ መሆኑንም ይናገራሉ። ከእንጦጦ እና አንድነት በተጨማሪ ወዳጅነት ፓርክም ቢሆን የተለያዩ ፕሮግራሞች እና ብዙ ሰርጎች እየተካሔዱበት መሆኑን ጠቅሰው፤ ቀን እና ማታ ሰዎች ስፖርት የሚሰሩባቸው እና ወላጆችም ልጆችን ይዘው የሚዝናኑባቸው ሁኔታዎች በስፋት ተፈጥረዋል ብለዋል። ይህ በቀጥታ ከቱሪዝም ጋር እንደሚገናኝ በማውሳት፤ የቱሪዝም ዘርፉ ዕድገት ከውጪ ብቻ ሳይሆን የሀገር ውስጥ ጎብኚዎችንም ያካተተ መሆን እንዳለበት ሊዘነጋ አይገባም ይላሉ።

ከውጪ ጎብኚዎች አንፃር ገበታ ለሸገር፣ እንጦጦ፣ አንድነትም ሆነ ወዳጅነት ገፅታን በመገንባት እና በበርካታ ሰዎች በመጎብኘት በገቢ ደረጃ በሚሰበሰብ ገንዘብ ሌሎች መዳረሻዎችን ማልማት ተጀምሯል። ይህ ትልቅ ተስፋ ሰጪ ጅምር ነው የሚል እምነት እንዳላቸውም አመላክተዋል።

ከቱሪዝም አንፃር ኢትዮጵያ ውስጥ ቱሪዝም ገና አዲስ ጅምር ነው። ዘርፉ የፖለቲካ ድጋፍ እና ትኩረት ማግኘት የጀመረው ገና አሁን ነው። አሁን ያለው ትኩረት ከቀጠለ ብዙ መዳረሻዎች እና መሠረተ ልማቶች መሠራት ይቻላል። ኢትዮጵያም ግብርና መር እና ኢንዱስትሪ መር ብቻ ሳይሆን ቱሪዝም መር የሆነ ትልቅ ኢኮኖሚን የምትገነባበት ሁኔታ ይፈጠራል ብለዋል።

በሌላ በኩል የዘርፉን ውጤታማነት ለመግለፅ ያህል ሚኒስትር ዴኤታው እንደተናገሩት፤ ብዙ የሥራ ዕድል ተፈጥሯል። የውጪ ምንዛሪ እየተገኘ ነው። በተጨማሪ አዲስ አበባ የአፍሪካ መዲና ናት እየተባለ ከሌሎች ከተማ ጋር ስትወዳደር የነበረችበት የሚታወስ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ እየኖሩ ያሉ የሌሎች ሀገሮች ሰዎች ማለትም የውጭ ዜጎች ሊዝናኑባቸው እና ሊኖሩባቸው የሚችሉባቸው ቦታዎች አልነበሩም፤ አሁን ግን በእግራቸው ሊንቀሳቀሱባቸው እና ሊዝናኑባቸው የሚችሉባቸው ቦታዎች ተፈጥረዋል። ይህም በራሱ ለቱሪዝም ዘርፉ ትልቅ ተስፋ ነው ብለዋል።

ከገበታ ለሸገር በተጨማሪ ገበታ ለሀገርም ወንጪ፣ ኮይሻ እና ሃላላ ኬላ በጣም በጥራት የተሰሩ ናቸው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ አሁን ላይ አንዳንዶቹ ምናልባት በቀላሉ ሰው ሊደርስባቸው የማይችሉባቸው ቢሆኑም፤ ለምሳሌ ጎርጎራ፣ ጨበራ እና ወንጪ ብዙ ሰው በቀላሉ ሊሔድ እና ሊጎበኛቸው ያሉበትንም ሁኔታ ማረጋገጥ እንደሚቻል ተናግረዋል። ሌሎቹም ቢሆኑ አንዳንድ የሰላም እጦት ያሉባቸው ቦታዎች እንዳሉ ሆነው የሰላም ሁኔታው ሲስተካከል ደግሞ በጣም በሰፊ ቁጥር መጎብኘት የሚቻልበት ሁኔታ እየተመቻቸ መሆኑን ተናግረዋል።

ከቱሪዝም ዘርፍ ጋር ተያይዞ ሚኒስትር ዴኤታው በደንብ መታወቅ አለበት ያሉት፤ የቱሪዝም አቅርቦት ለዘመናት የተዘነጋ ክንፍ መሆኑን ነው። «ብዙ ጊዜ ምን ያህል ቱሪስት መጣ ይባላል። ይህ የፍላጎት ጉዳይ ነው። ትልቁ ሥራ ግን አቅርቦት ነው። መጀመሪያ የሚጎበኝ መስዕብ፣ ወይም መዳረሻ ምን ያህል ተሠራ? የሚል ጥያቄ መጠየቅ ያስፈልጋል። ቱሪስቱ የሚፈልገውን ነገር በቅርቡ ያገኛል? አስፈላጊው መሠረተ ልማት ተሟልቷል? በዘመናዊ መልኩ የሠለጠነ፣ የበቃ፣ ዕውቀት እና ሥርዓት ያለው የሰው ኃይል አለ? በየቦታው ምቹ የጉብኝት ሥርዓት አለ? » የሚሉት ጉዳዮች ተረስተው ቆይተዋል ብለዋል።

ዘርፉ ላይ በአቅርቦት ላይ በስፋት ባለመሠራቱ ፈተናው ውስብስብ ሆኖ ቆይቷል። ነገር ግን አሁን ብዙ ገንዘብ የሚጠይቁ እነዚህ ጉዳዮች በስፋት እየተሠራባቸው መሆኑን አመላክተዋል። የቱሪዝም አቅርቦቶች ረዥም ጊዜ ይወስዳሉ። ከፍተኛ አቅም እና እውቀት የሚፈልጉ ናቸው። ነገር ግን አቅርቦቶች ከተሟሉ መዳረሻዎች በቀላሉ በቱሪስቶች የመመረጥ ዕድል እንደሚኖራቸው ተናግረዋል።

የጎበኙ ሰዎች ደግሞ ተደስተው ሌሎች እንዲያዩት ለመናገር የሚችሉበት ዕድል ይፈጠራል። ስለዚህ አሁን እየተሠራ ያለው ሥራ ከማስተዋወቅ ጋር ተያይዞ በቀላሉ ውጤት ለማምጣት የሚያስችል ነው ማለት ይቻላል ብለዋል። አገልግሎት ላይ በዓይነት፣ በጥራት በጣም በተቀናጀ እና በተደራጀ መልኩ እየተሠራ ነው፤ ስለዚህ ምንም እንኳ የቱሪዝም ዘርፉ በብዙ ፈተናዎች ውስጥ ቢያልፍም አሁን ትልቅ ተስፋ አለው የሚል እምነት እንዳላቸው አመላክተዋል።

እንደ አስተያየት ሰጪዎቹ ገለፃ፤ ኢትዮጵያ በዩኔስኮ የተመዘገቡትን ቅርሶች ጨምሮ ብዙ ሀብቶች አሏት። ሕዝቡ የሚያከብራቸው ብዙ በዓሎች አሉት፤ በተጨማሪ ባሕሉን ጠብቆ የሚኖር መሆኑም ይታወቃል። እነዚህን ሀብቶች በአግባቡ ማስተዋወቅ ከተቻለ እና መሠረተ ልማቶች በአግባቡ ከተሟሉ እንዲሁም የግጭቶች ጉዳይ መፍትሔ ከተበጀላቸው ሀገሪቱ በብዙ ጎብኚዎች የማትታይበት ምክንያት የለም። አብሮ መዳረሻዎችን በስፋት ማልማት ከቀጠለ እና አቅርቦት ላይ በስፋት ከተሠራ ከቱሪዝም ዘርፉ የሚፈለገውን ገቢ ማግኘት ይቻላል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# በልጅነት እድሜ ለትምህርት የተከፈለ ዋጋ

አመለወርቅ ከበደ

ገና በልጅነት እድሜዋ ነበር ከምትኖርበት ቤት ጠፍታ ትምህርትን ፍለጋ የወጣችው። ለትምህርት ስትል በነበረችበት አካባቢ ገና በለጋ እድሜዋ አቅሟ የማይፈቅደውን ሥራ ሰርታለች። የሚደርሱባትን ጫናዎች ሁሉ ተቋቁማ ትምህርቷን ለመቀጠል ብትጥርም አሳዳጊ አጎቷ እንድትማር ፍላጎት ስለሌለው የተወለደችበትን ቀዬ ጥላ ለመጥፋት ተገደደች።

አፋር ክልል በመሄድ ከቤት ሠራተኝነት አንስቶ ሌሎች ሥራዎች እየሰራች ለመማር ብትሞክርም ፤ ሁኔታዎች ስላልተመቿት ጥላ ወደ አዲስ አበባ ከተማ መጣች። አዲስ አበባም ሰው ቤት ተቀጥራ እየሰራች ትምህርቷን ለመቀጠል ብትሞክርም፤ ካለባት የጤና ችግር ጋር ተያይዞ መሥራት ተቸገረች። ይህም ሁኔታዋ አስገድዷት ወደ ጎዳና ልትወጣ ስትል ነበር ወደ ለነገዋ የሴቶች ተሃድሶ ማዕከል የመግባት እድል ያገኘችው።

የዛሬዋ የሴቶች እንግዳችን ምትኬ መኮንን ትባላለች የ20 ዓመት ወጣት ናት። ትውልድና እድገቷ በኦሮሚያ ክልል ኢሉ አባቦራ ነው። ወላጆቿን ያጣችው በጨቅላ እድሜዋ በመሆኑ አጎቷ ጋር ነው ያደገችው። ምትኬ አጎቷ መማሯን ባለመውደዱ እና ለትምህርት ካላት ከፍተኛ ፍቅር የተነሳ እራሷን ለማስተማር ስትል ከአጎቷ ቤት የወጣችው በ12 ዓመቷ ነው።

“የእናትና አባቴን መልካቸውን እንኳን አላውቀውም፤ ያሳደገኝ አጎቴ ነው። አጎቴ ደግሞ ሊያሳድገኝ እንጂ፤ ሊያስተምረኝ ፈቃደኛ አይደለም። ” የምትለው ምትኬ አሁን ላይ የ10ኛ ክፍል ተማሪ እንደሆነች በመግለጽ፤ ወደዚህ የክፍል ደረጃ የደረሰችው እራሷን በማስተማር እንደሆነ ትናገራለች።

“አንደኛ ክፍል ስገባ አንድ ደብተር ብቻ ነበር አጎቴ የገዛልኝ። በዛ ላይ ደግሞ በባዶ እግሬ ነበር ረጅም እርቀት የምጓዘው። አንደኛ ክፍል ጨርሼ ወደ ሁለተኛ ክፍል ስሻገር፤ ክረምት ላይ ሥራዎችን በመሥራት ለደብተር እና ለእስክሪብቶ የሚሆን ገንዘብ መሥራት ጀመርኩ። ከዛን መስከረም ሲደርስ የትምህርት ቁሳቁሶቼን እራሴ ነበር የምገዛው። ”

“አዲስ አበባ ከመምጣቴ በፊት ኢሉ አባቦራ እያለሁ ትምህርቴን እየተማርኩ የቀን ሥራ እሰራ ነበር።” የምትለው ባለታሪኳ፤ በቡና ማሳ ላይ የቡና ጉድጓድ በመቆፈር እና በምንጣሮ ሥራ ተሰማርታ ትሰራ እንደነበር ትገልጻለች። ምትኬ በለጋ እድሜዋ ነበር ለደብተር እና እስክርብቶ መግዣ ብር ለማግኘት ያልሰራችው ሥራ አልነበረም።

ክፍለ ሀገር በነበረችበት ጊዜ ረጅም መንገድ በእግሯ ተጉዛ ነበር ትምህርት ቤት የምትደርሰው። “ኢሉ አባቦራ በነበርኩበት ወቅት ትምህርት ቤቱ ሩቅ ስለነበር ትምህርቴን ለመከታተል በቀን የአንድ ሰዓት መንገድ በባዶ እግሬ መጓዝ ይጠበቅብኝ ነበር። በባዶ እግሬ ስለሆነ የምጓዘው ፀሐይ በሚሆንበት ወቅት ጠጠሩ እግሬን እያቃጠለኝ ነበር የምማረው። ”ትላለች።

ምትኬ ብዙ ጊዜ የትምህርት ቁሳቁሶቿን ለመሸፈን የቀን ሥራዎችን የምትሰራው፤ የመጀመሪያው አጋማሽ አልቆ ባለው የዕረፍት ጊዜ እና ክረምት ወቅት ላይ ነበር። ወደ ትምህርቷ እና ሥራ ከመሄዷ በፊትም ቤት ውስጥ ያለውን ሥራ መሥራት ይጠበቅባታል። “እንጨት ለቅሜ፣ ለከብቶች የሚያስፈልገውን አሟልቼ፣ ውሃ ቀድቼ ነው ወደ ሥራ የምሄደው። ከሥራ ስመለስም እንደዛው እሰራለሁ። ” ስትል ትገልጻለች።

ምትኬ ትምህርቷ እንድትገፋ ማንም የሚረዳት ሰው ባለመኖሩ የተሻለ ነገር ፍለጋ ካለችበት አካባቢ ጠፍታ ወደ አፋር ክልል ሄደች። “ዘመዶቼ እያሉ የቀን ሥራ እየሰራሁ መማሬ በጣም አናደደኝና ተምሬ እራሴን መለወጥ እንዳለብኝ ለእራሴ በመንገር ወደ አፋር ሄድኩኝ። ”ስትል ትገልጻለች።

የአጎቷ ጥገኛ ሆና መቅረት እንደሌለባት ወስና ከቤት መውጣቷን የምትናገረው ባለታሪኳ፤ አጎቷ አንደኛ ክፍል እንኳን ያስገባት የሰዎች ከፍተኛ ግፊት ስላስገደደው ነበር። እንጂ በጭራሽ ምትኬ እንድትማር እንደማይፈልግ ትናገራለች። ምትኬ ትምህርቷን አጥብቃ የመፈለጓ ምክንያት ቤተሰብ የሌላት እንደመሆኗ ሊያልፍላት የሚችለው በትምህርቷ ብቻ መሆኑን ታምናለች። ያላት ብቸኛ አማራጭም ችግሮችን ተጋፍጦ ጠንክሮ መማር ብቻ ነበር።



ምትኬ መኮንን

አፋር ከሄደች በኋላ መጀመሪያ ላይ በአንድ ደላላ አማካኝነት ሰው ቤት ተቀጥራ መሥራት ብትጀምርም፤ ኩላሊቷን ስለሚያማት በምትሰራበት ቤት መቀጠል አልቻለችም። ” አፋር ላይ መጀመሪያ ሰው ቤት እየሰራሁ ቀስ በቀስ አንዳንድ እቃዎች ከአንድ ሱቅ ወደ አንድ ሱቅ እየወሰድኩ እያከፋፈልኩ መሥራት ጀመርኩ። ነገር ግን የአካባቢው ሙቀት በጣም ከፍተኛ ስለነበር አልቻልኩም። በዛ ላይ ደግሞ አፋር እንኳን የማታ ትምህርት፤ የቀን ትምህርት ቤቶች እንኳን ለማግኘት ከባድ ነው። ” ትላለች።

አፋር ከጤናዋ ጋር ተያይዞ ሙቀቱን መቋቋም እንዳልቻለች እና ትምህርቷንም አንድ ዓመት ልታቋርጥ ግድ ሆኖባት ነበር። በእነዚህ ምክንያቶች ልትቆይ የቻለችው ለስምንት ወራት ያህል እንደሆነ የምትናገረው ባለታሪኳ፤ “ትኬት ቆረጥኩና ቀጥታ ወደ አዲስ አበባ መጣሁ። ” ስትል ሁኔታውን ታስረዳለች።

አዲስ አበባ መጥቼ አንድ ሆቴል እየሰራሁ ነበር፤ ከዛም ወጣሁና እጄ ላይ ገንዘብ ስለነበረኝ አልጋ ቤት እያደርኩ፤ ሌላ ቤት ለመቀጠር ጥረት ማድረግ ጀመርኩ። ሆኖም ግን የጤናዬ ጉዳይ ስለሚያሳስበኝ ሥራውን ትቼ ጎዳና ልወጣ ስል ነበር ወደ ነገዋ የሴቶች ማዕከል የመግባት እድሉን ያገኘሁት። ” ስትል ትገልጻለች።

ምትኬ ሰው ቤት ተቀጥራ ከመግባቷ አስቀድማ ትምህርቷን እንድትማር ፈቃደኛ መሆናቸውን ጠይቃ ከተስማሙ ነው የምትገባው። ቀን እየሰራች፤ የምትማረው ማታ ነው። “እንደዛም ስማር እያረፈድኩ፣ እየቀረሁ ነው የምማረው። በትምህርቴ ደህና የምባል ዓይነት ተማሪ ነኝ። አንድ ቀን ከትምህርቴ ከቀረሁ እኔ የቀረሁበት ቀን ምን እንደተማሩ ከተማሪዎች ሆነ ከመምህራኖች ጠይቄ ለመረዳት እሞክራለሁ። ” ትላለች።

ወደ ነገዋ የሴቶች ማዕከል የገባችበትን አጋጣሚ ስትናገር አንድ ከምትተዋወቀው ሰው ጋር በሚያወሩበት ወቅት ስለ ማዕከሉ አንስቶ እንደነገራት ትናገራለች። ” እንደዚህ ዓይነት ማዕከል አለ ገቢና እራስሽን ለውጭ አለኝ። ትምህርት መማር እፈልጋለሁ፤ የትምህርቴ ጉዳይ ምን ይሆናል? ብዬ ስጠይቀው፤ ገና ልጅነሽ ወደ ማዕከሉ ገብተሽ ስልጠናውን አጠናቀሽ ስትወጪ ትምህርትሽን ትቀጥያለሽ ብሎ መከረኝና ተስማማሁ። ” ትላለች።

“ወደ ነገዋ የሴቶች ማዕከል ስመጣ ሰውዬው እንደነገረኝ ሁሉም ነገር የተሟላ ነበር። መጀመሪያ ላይ

> ምትኬ ትምህርቷን አጥብቃ የመፈለጓ ምክንያት ቤተሰብ የሌላት እንደመሆኗ ሊያልፍላት የሚችለው በትምህርቷ ብቻ መሆኑን ታምናለች:: ያላት ብቸኛ አማራጭም ችግሮችን ተጋፍጦ ጠንክሮ መማር ብቻ ነበር

ለ10 ቀናት የክህሎት ስልጠና ተሰጠን፤ ከዛን ወደ ሙያ ስልጠና ገባን። በመሀልም እንደዚያው የክህሎት ስልጠና ተሰጥቶናል። ” የምትለው ምትኬ፤ የሰለጠነችው በቧንቧ እና ኤሌክትሪክ ሙያ ነው። መጀመሪያ ላይ ጨርቃጨርቅ ላይ ስልጠና መውሰድ ፈልጋ የነበረ ቢሆንም፤ በአጋጣሚ በቧንቧ ሙያ ላይ ከሚያስተምር መምህር ጋር ተገናኝተው በቧንቧ ብትማር ጥሩ እንደሆነ ነግሯት እንደቀየረች ታስረዳለች።

“እኔ የመረጥኩት በቧንቧ ሙያ ቢሆንም፤ ቧንቧ ላይ እኔ ብቻ ስለሆንኩ ያለሁት ተማሪ ፤ እንዴት ሆኜ ነው ብቻዬን የምማረው ብዬ እያሰብኩ እያለ፤ ኤሌክትሪክ እና ቧንቧ አንድ ላይ እንዲሰጥ ተደረገ። በወሰድኩት ስልጠና በጣም ደስተኛ ነኝ። “የምትለው ባለታሪኳ ከዚህ በፊት ወንዶች ብቻ የሚሰሩበት ሙያ አድርጌ አስብ ነበር ስትል ትናገራለች።

“ከዚህ በፊት በዚህ ዘርፍ የሚሰሩ ሰዎችን ስመለከት መሞከር እፈልግ ነበር። ነገር ግን ሳይት ላይ ስለሆነ የሚሰሩት አልቻልኩም። ስልጠናውን ስወስድ አልከበደኝም፤ በጥሩ ሁኔታ ነበር የተከታተልኩት። ”ትላለች።

በማዕከሉ ገብታ ያየቻው እና የተማረችው ነገር በጣም እንዳስደሰታት የምትናገረው ምትኬ፤ ከዚህ በፊት እንደዚህ ዓይነት ነገር አይቼ አላውቅም። በወሰደችው የሕይወት ክህሎት ስልጠና ሰዎችን መርዳት፣ መታዘዝ እንዴት እንዳለባት፤ የወደፊት ህልሟን ለማሳካት ምን ማድረግ እንዳለባት እና ሌሎች ብዙ ነገሮችን ከስልጠናው ማግኘቷን ታስረዳለች።

ባለታሪኳ ወደ ማዕከሉ በመግባቷ ትልቅ ትምህርት እንዳገኘች በመግለጽ፤ “እስካሁን ከወሰድኩት ስልጠና በማዕከሉ ትልቅ ትምህርት ማግኘት ችያለሁ። የተሰጠን የሕይወት ክህሎት ስልጠና ብዙ ነገር እንድማር አድርጎኛል። ከዚህ በፊት ትዕግስት አልነበረኝም፤ ታክሲ እንኳን ቆሜ ለመጠበቅ ትዕግስት ስለማጣ እየተራመድኩ ነበር የምጠብቀው። ” የምትለው ባለታሪኳ አሁን ላይ በወሰደችው የሕይወት ክህሎት ስልጠና መሻሻሏን እና ከሰዎች ጋር ያላት ተግባቦትም ማሳደጓን ታስረዳለች።

“ወደ ማዕከሉ ከመግባቴ በፊት ውጭ ላይ ከብዙ ሰዎች ጋር እግባባለሁ። ምንም እንኳን ችግረኛ ብሆንም ስለምታዘዝላቸው ብዙ ሰዎች ይወዱኛል። ይህን ሳስብ ወደ ማዕከሉ ለመምጣት ፈርቼ ነበር፤ የበለጠ ያሳሰበኝ ግን የትምህርቴ ጉዳይ ነበር። ” ትላለች።

የኩላሊት ህመሟ አሁን በጥሩ ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ የምትገልጸው ምትኬ፤ “ፀበል እጠቀማለሁ፣ ውሃም በበቂ ሁኔታ እጠጣለሁ። በዛ ላይ እንቅስቃሴ ስለማድረግ ፈጣሪ ይመስገን ደህና ነኝ። ” ስትል ያለችበትን የጤና ሁኔታ ታስረዳለች።

“ቀጣይ እቅዴ በሰለጠንኩት የስልጠና ዘርፍ እየሰራሁ ትምህርቴን መቀጠል ነው። የወደፊት ምኞቴ ብዙ ነው። በሰለጠንኩት ሙያ ትምህርቴን ከቀጠልኩ መሐንዲስ ነው የምሆነው፤ እንደዛም መሆን እፈልጋለሁ፤ ነገር ግን የበለጠ መሆን የምፈልገው መምህር ነው። ”ትላለች።

“አንድ መምህር በሚሰጠው ትምህርት ተማሪ ሰፊ እውቀት ያገኛል። እኔ አንድ መምህር ሲያስተምር በደንብ ነው የምከታተለው፤ ወደፊትም ጥሩ መምህር የመሆን ህልም አለኝ። ጥሩ ዕውቀት ቀስሜ ተመልሼ ሌሎችን በማስተማር ባለኝ እውቀት ሌሎችን መርዳት እፈልጋለሁ። ” ስትል ትናገራለች።

ችግር ውስጥ ያሉ ሴቶች መንግሥት የሚሰጣቸውን ዕድል ሊጠቀሙበት ይገባል የምትለው ምትኬ የነገዋ የሴቶች ማዕከል ብዙዎችን ከጎዳና እያነሳ ሰው እያደረገ መሆኑን ትናገራለች። “እኔ ትምህርት ለመማር ብፈልግም እድሉን በመከልከሌ ከአሳዳጊዮቼ ቤት ልወጣ ተገድጃያለሁ። ” የምትለው ምትኬ፤ እንደሷ ትምህርት ለመማር አብዝተው የሚፈልጉ ሴቶችም በሁኔታዎች ተስፋ ሳይቆርጡ ካሰቡበት መድረስ እንደሚችሉ ካላት የሕይወት ልምድ በመነሳት መልዕክቷን ታስተላልፋለች።

“ለተደረገልኝ ነገር በቅድሚያ ፈጣሪን አመሰግነዋለሁ፤ በመቀጠል ከንቲባ አዳነች አቤቤን ላመሰግን እወዳለሁ። ምክንያቱም የተደረገልኝ ነገር እናት እራሱ የምታደርገው አይመስለኝም። ”የምትለው ምትኬ በተጨማሪም ባለታሪኳ በማዕከሉ ለሚያገለግሉ አስተዳደር አካላት፤ ለስፖርት አሰልጣኞች፣ ለመምህራን እና ለሌሎች አካላት ምስጋናዋን አቅርባለች።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ግርማ መንግሥቴ

አዲስ ዘመን ዛሬም እንደ ቀድሞው ሁሉ ታሪክን ሊያስኮመኩመን ከተፍ ብሏል። የዛሬው እንደ ምን ጊዜውም የድሮውን አቅርቦ የሚያሳይ ቢሆንም ለየት የሚያደርገው ጉዳይ ግን አለ፤ እሱም እንስትዋን የኮንጎ ዘማችን ገድል ይዞ መቅረቡ ነው።

ብዙ ጊዜ ሲነገር እንደምንሰማው በኮንጎም ሆነ ሌሎች ኢትዮጵያ የተሳተፈችባቸው የሀገራትን ሠላም የማስከበር ሥራዎች የወንዶች ተሳትፎና ኢትዮጵያዊ ጀግንነት እንጂ የሴቶቹ የድል ብስራትና የጦር ሜዳ ውሎ ብዙም ሲነገር አይሰማም። ይሁን እንጂ በአስደማሚ ሁኔታ ግዳጃቸውን የፈፀሙ እንስቶች በርካቶች መሆናቸው የሚታወቅ ቢሆንም፣ ለዛሬ ግን አንዷን እናስታውስ፡፡

የፀሐይ ግርዶሽን በተመለከተም ለየት ያለ ታሪክን የምናገኝ ሲሆን፣ ለጉዳዩ ይሰጥ የነበረውን ትኩረት ብቻም ሳይሆን በዛን ዘመን ጉዳዩ እነማንን ይመለከት እንደነበርም ያስገነዝባልና የዛሬው "አዲስ ዘመን ድሮ" ለየት ያለ ነው።

**ኪራይ ቤት እፈልጋለሁ**

ዛፎች ያሉበት ትልቅ ጊቢ ውስጥ ሰፊ ሳሎን ያለው ቤት እፈልጋለሁ።

**ስልክ ቁጥር 2920**

**(አዲስ ዘመን፣ ሐምሌ 12 ቀን 1951 ዓ.ም)**

**ቆራጥዋ ሻምበል አስቴር አያና በኮንጎ የፈፀመችው ሙያ**

የኮንጎን ፀጥታ ለማስከበር በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት መልካም ፈቃድ ከተላኩት የጠቅል ብርጌድ ወታደሮች አንድዋ ቆራጥዋ ሻምበል አስቴር አያና ናት። ሻምበል አስቴር አያና እድሜዋ 25 ሲሆን፣ ወደ ኮንጎ የተላከችውም የህክምና ርዳታ እንድታደርግ ነው። ይህች ወጣት ባለፉት ጊዜያቶች ለፈፀመቻቸው አስመስጋኝ ሙያዎች መሪ የሆናትን የነርስነት ትምህርት የተማረችው በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሆስፒታል ነው።

ከዚህም በቀር ወደ ጀርመን ሀገር ሄዳ የአዋላጅነት ትምህርት ተምራለች። በዚሁም ትምህርቷ ተመርጣ የቃኘው ሻለቃ ጦር በሩቅ ምሥራቅ የተናጋውን የኮሬን ሠላም ለመመለስ በዘመተ ጊዜ በመቶ አለቅነት ማእረግ ዘምታ ቁስለኞችን በማከምና በማስታመም ግዳጅዋን ፈፅማለች።

ስለዚህም ያገልጋዮቻቸውን ውለታ ከማያስቀሩት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት እጅ የአገልግሎት ሜዳይ ተሸልማለች። ከኮሬ ጦር ግንባር እንንደ ተመለሰችም በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ሆስፒታል ውስጥ ሁና ኢትዮጵያውያን ወገኖችዋን ባላት የህክምና እውቀት አገልግላለች።

ይህንን በመሳሰለው ቅን አገልግሎት የፈፀመችው ሲስተር አስቴር አያና በግርማዊነታቸው መልካም ፈቃድና ትእዛዝ ወደ ኮንጎ ሬፐብሊክ ከተላከው ጠቅል ብርጌድ ጋር በሻምበልነት ማእረግ ሄዳ ስለነበር ለንጉሠ ነገሥቷ ክብር፣ ለሀገሯ ኩራት የሚሆን ተግባር ፈፅማለች።

ኮንጎ በሚገኙት የተባበሩት መንግሥታት ወታደሮች ላይ የኮንጎ ወታደሮች በፈፀሙት የግፍ ድብደባ ጊዜ ሻምበል አስቴር አያና ተደብዳቢዎችን የተባበሩት መንግሥታት ወታደሮችን ለማዳንና ፀቡን ለማብረድ የተቻላትን ያህል ከደከመች በኋላ የጠቅል ብርጌድ ወታደሮችን ርዳታ ጠርታ አድናቸዋለች፤ ይህም ሙያዋ ዝነኛነትንና ተደናቂነትን ያተረፈላት ከመሆኑም በላይ፤ የኢትዮጵያውያትን ጀግንነት በውጭ ሀገር ለማስመስከር ምሳሌ ሁናለች።

**(አዲስ ዘመን፣ ነሀሴ 25 ቀን 1952 ዓ.ም)**

**የፀሐይ ግርዶሽ**

ከዚህ ቀደም ወደ ፊት መስከረም 21 ቀን ስለሚደረገው የፀሐይ ሙሉ ግርዷ ከትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር በደረሰን መሠረት አንባቢዎቻችን ይህን ቀን እንዲያውቁት ገልፀን ነበር።

የዚህም የፀሐይ ኤክሊፕስ ጊዜው ከመድረሱ አስቀድሞ ተመልካቾች የሆኑት ሁሉ ሊያደርጉት የሚገባቸውን ጥንቃቄ በመግለፅ የትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ምክር ሰጥቷል።

የፀሐይን ግርዷ የሚመለከቱ ሰዎች ሁሉ ዘለአለማዊ የአይን ጉዳት እንዳይደርስባቸው በጭስ የጠቆረ መስተዋት አማካይነት ለማየት መጠቀም እንደሚችሉና ይህን ባያደርጉ የአይን ጉዳት የሚያገኛቸው መሆኑን አስጠንቅቋል።

በተለይም በአዲስ አበባና በሻሸመኔ አካባቢ ነዋሪ የሆኑ ግርዷውን ለማየት የሚችሉት በዚህ ዘዴ መሆኑንና መቶ በመቶ የሚሆነውን የፀሐይ ግርዷ ፎቶግራፍ ለማንሳት ደግሞ ጥሩ ጥሩ ፎቶግራፍ ማንሻ ያሉዋቸው ሰዎች ሻሸመኔ ድረስ ቢሄዱ አስረጅነት ያለው ፎቶግራፍ ማንሳት የሚችሉ መሆናቸውን ጭምር ገልፆል።

**(አዲስ ዘመን፣ መስከረም 15 ቀን 1952 ዓ.ም)**

**የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ኦብዘርቫቷር አባሎች ወደ ሻሸመኔ ሄዱ**

ዛሬ መስከረም 21 ቀን 1952 ዓ/ም ከእኩለ ቀን በላይ ስለሚሆነው የፀሐይ ግርዷ ሁኔታው ሙሉ በሙሉ ወደሚታይበት ወደ ሻሸመኔ ከተማ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ኦቭዘርቫቷር መሪና የሥራው ተካፋይ ከሆኑት ኢትዮጵያውያን ጋር አስፈላጊውን የምርመራና የፎቶግራፍ ማንሻ መሣሪያዎች ይዘው መስከረም 20 ቀን 1952 ዓ/ም ትናንት ወደ ሻሸመኔ ሄዱ።

**(አዲስ ዘመን፣ መስከረም 21 ቀን 1952 ዓ.ም)**

**መግለጫ**

የደግን ሰው ሥራ የሚያስታውስ፣ ህሙማንን ከስቃያቸው የሚፈውስ አንድ ሆስፒታል ለማሠራት የአስተዋፅኦ ገንዘብ ከመላው ኢትዮጵያና ከውጭ ሀገር ሳይቀር በብዛት ሲሰበሰብ ይታያል።

ይህም ለስመ ጥሩ መስፍን ልኡል መኮንን አልጋወራሽ ኃይለሥላሴ መታሰቢያ፣ ለሕዝብ መጠቀሚያ እንዲሆን ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በፈለቀው በጎ ፈቃድ የሚሠራው ሆስፒታል መሆኑ ግልፅ ነው።

በዚህም መሠረት ለመታሰቢያው መሥሪያ የሚሰበሰበው ገንዘብ ከምን እንደደረሰ በየ ሳምንቱ ከመገለፅ አላቋረጠም፤ አሁንም ይህ ከእለት እለት ከፍ እያለ የሚሄደው የርዳታ ገንዘብ እስከ ሚያዚያ 30 ቀን 1951 ዓ.ም ድረስ 3,194,750.05 (ሶስት ሚሊዮን አንድ መቶ ዘጠና አራት ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ ብር ከዜሮ አምስት ሳንቲም) የደረሰ መሆኑን እናስታውቃለን።

**የልዑል መኮንን መታሰቢያ ድርጅት ዋና ጽሕፈት ቤት**

**(አዲስ ዘመን፣ ግንቦት 3 ቀን 1951 ዓ.ም)**

# ዓለም አቀፍ

## በመካከለኛው ምሥራቅ ያንዣበበው ስጋት

በጋዜጣው ሪፖርተር

እስራኤል በሊባኖስ ውስጥ በሚገኙ ዒላማዎች ላይ ባለፈው ሳምንት የጀመረችው የአየር ጥቃት አርብ ላይ ለሄዝቦላህ ከባድ ጉዳት ሲያስከትል ለእስራኤል ደግሞ ወሳኝ የተባለ ግዳይ ጥሎላታል።


በጥቃቱ የሄዝቦላህ መሪ ሐሳን ናስራላህን እና ተጨማሪ 20 የቡድኑን ከፍተኛ አመራሮችን መግደሏን እስራኤል ስትገልጽ፣ ሄዝቦላህም ቁጥር ሳይጠቅስ መሪው እና ሌሎች አመራሮቹ እንደተገደሉበት አረጋግጧል።

እስራኤል ሊባኖስ ውስጥ እየፈጸመችው ባለው የአየር ጥቃት የተገደሉት የሄዝቦላህ መሪዎች ብቻ ሳይሆኑ የደጋፊው ኢራን አብዮታዊ ዘብ ከፍተኛ ጄኔራል እንዲሁም የፍልስጤሙ ቡድን ሐማስ አመራር መገደላቸውን ከአርብ በኋላ ባሉት ቀናት የወጡት መረጃዎች ያመለክታሉ።

በጋዛ ጦርነት አንድ ዓመት ለሚጠጋ ጊዜ በውጥረት ውስጥ የቆየው የመካከለኛው ምሥራቅ አካባቢ ውጥረት እስራኤል በሊባኖስ ላይ እያካሄደችው ባለው ጥቃት የበለጠ ተባብሷል። በተለይ የሄዝቦላህ መሪ መገደል በሊባኖስ እና በኢራን ውስጥ ከፍተኛ ቁጣን የቀሰቀሰ ሲሆን፣ ግጭቱ የበለጠ ሊስፋፋ ይችላል የሚል ስጋትን አስከትሏል።

እስራኤል በተጨማሪም የየመን ታጣቂ ቡድን የሆነውን የሁቲ ይዞታዎችን ዕሁድ ዕለት በአየር በመደብደብ የጥቃት አድማሷን የበለጠ አስፍታዋለች። በጥቃቱ የኢራን የጦር መሣሪያ ድጋፍ የሚተላለፍባቸው የመን ውስጥ የሚገኙ ወደቦች ዒላማ መሆናቸውን የእስራኤል ሠራዊት አስታውቋል።

የእስራኤል የመከላከያ ሚኒስትር ዮአቭ ጋላንት በሁቲ ይዞታዎች ላይ ከተፈጸመው የአየር ጥቃት በኋላ በሰጡት መግለጫ "[በጥቃቱ] ማስተላለፍ



የፈለግነው መልዕክት ግልጽ ነው፤ ለእኛ [ለእስራኤል] የትኛውም ቦታ ለመድረስ ሩቅ አይደለም" በማለት ጠላቶቻቸውን ባሉበት ቦታ ዒላማ እንደሚያደርጉ አሳውቀዋል።

እስራኤል በሐማስ ጥቃት ከተፈጸመባት በኋላ በጋዛ ላይ እያካሄደችው ያለው ዘመቻ መቋጫ ሳያገኝ አሁን ከሄዝቦላህ ጋር ገጥማለች። በተጨማሪ ደግሞ ርቆ ከሚገኘው የየመኑ ቡድን ሁቲ ጋርም እንዲሁ ሌላ ግንባር ከፍታለች። ስለዚህም በአንድ ጊዜ ሁሉንም ጠላቶቿን በመግጠም ከባድ ጦርነት ውስጥ ገብታለች።

እስራኤል በሄዝቦላህ መሪ ላይ የፈጸመችው ግድያ ወሳኝ ርምጃ መሆኑን የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትር ቤንያሚን ኔታኒያሁ በሀገራቸው ውስጥ የተዳከመው ድጋፋቸውን እንዲያንሠራራ እንዳደረገው ምልክቶች እየታዩ ነው።

ምዕራባውያን ወዳጆቻቸውም ሽብርተኛ የሚሉት ቡድን አመራሮች ላይ በወሰደችው ርምጃ ድጋፋቸውን በግልጽ እና በዝምታ ገልጸዋል። የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን በናስራላህ ቡድን ጥቃት ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች "ፍትህን የሚሰጥ ርምጃ" በማለት አወድሰውታል።

የሄዝቦላህ ዋነኛ ወዳጅ እና ደጋፊ የሆነችው ኢራን በቡድኑ አመራሮች ላይ ከተፈጸመው ግድያ በተጨማሪ ከፍተኛ የጦር መኮንኗ የተገደሉባት ሲሆን፣ የበላይ መሪዋ አያቶላህ አሊ ኻሜኒ የእስራኤል ጥቃት የበቀል ምላሽ እንደሚጠብቀው ዝተዋል።

እስራኤል በዙሪያዋ ያሉ ጠላቶቿ የሆኑ ታጣቂ ቡድኖች ላይ መጠነ ሰፊ ጥቃት በማካሄድ መሪዎቻቸውን ዒላማ ባደረገችበት በዚህ ወቅት የሁሉም ቡድኖች ደጋፊ እና አስታጣቂ የሆነችው ኢራንም ስጋት የገባት ይመስላል። በዚህም መሪዋን አሊ ኻሜኒ ደህንነቱ ወደ ተጠበቀ ሥፍራ እንዲዘዋወሩ መደረጋቸው ተነግሯል።

ከሁሉ አሳሳቢ የሆነው ባለፈው የሐማሱ መሪ በዋና ከተማዋ ቴሄራን በተገደሉበት ጊዜ በእስራኤል ላይ የበቀል ርምጃ እንደምትወስድ የዛተችው ኢራን አሁን የበለጠ ስጋት ውስጥ ከገባች በእስራኤል ላይ ቀጥተኛ ጥቃት ልትፈጽምና የግጭቱ እና የቀውሱ አድማስ ሊስፋፋ ይችላል የሚል ነው።

የኢራን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቃል አቀባይ እንዳሉት ምንም እንኳን ሀገራቸው ጦርነት ውስጥ መግባት ባትፈልግም ጦርነትን አትፈራም በማለት የእስራኤል "የወንጀል ድርጊት" በኢራን በኩል ምላሽ እንደሚሰጠው መናገራቸውን ሮይተርስ ዘግቧል።

የእስራኤል ጥቃት እያየለ የኢራንን ወዳጆች እያዳከመ ባለበት በአሁኑ ወቅት፤ ቀጣይ ዒላማ እሷ ልትሆን እንደምትችል ኢራን ስጋት ሊገባት ይችላል። በተለይ ኢራን ለዓመታት በመካከለኛው ምሥራቅ በመደገፍ ያጠናከረቻቸው ቡድኖች በእስራኤል ጥቃት መዳከም እና የትም የሚደርሱ አለመሆናቸው ሌላ አማራጭ እንድትፈልግ ሳያደርጋት አይቀርም።

በዚህም ምክንያት ለዘመናት ስትታማበት ወደነበረው የኑክሌር ጦር መሣሪያ ፊቷን ልታዞር ትችል ይሆን የሚል ጥያቄ እየተነሳ መሆኑን የቢቢሲ ዓለም አቀፍ አርታዒ ጄሬሚ ቦዌን ይጠቅሳል። ነገር ግን ይህ ውሳኔዋ የበለጠ አደገኛ ውጤትን ይዞ ሊመጣ እንደሚችል አመልክቷል።

ኢራኖች የኑክሌር ጦር መሣሪያን በተመለከተ አስፈላጊውን የቴክኒክ ዕውቀት በእጃቸው ለማስገባት መቃረባቸው ይታመናል። ለጥቃት ሊውል የሚችልበት ዕድል ካለ እና በትክክል ከታወቀ ኢራን የአሜሪካ የቦምብ ጥቃት ዒላማ ልትሆን የምትችልበት ዕድል ሰፊ ነው። ይህ ነው እንግዲህ ቀጣናውን ብሎም ዓለምን እያሳሰበ ወዳለ ከባድ ቀውስ ሊመራ ይችላል የሚል ስጋትን የፈጠረው።

አሁን የእስራኤል የአየር ጥቃት ዒላማ በሆነችው ሊባኖስ ውስጥ ባለፉት ሁለት ሳምንታት በየዕለቱ በተፈጸሙ ጥቃቶች ከአንድ ሺህ በላይ ሰዎች መገደላቸውን እና አንድ ሚሊዮን የሚደርሱ ሰዎች መፈናቀላቸውን የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ናጂብ ሚካቲ አስታውቀዋል።

እስራኤል በሊባኖስ ውስጥ እያካሄደችው ያለው ጥቃት ዒላማ ያደረገው ሄዝቦላህን ነው ብትልም በርካታ ሰላማዊ ሰዎች ላይ ጉዳት እየደረሰ መሆኑን የሚወጡ ሪፖርቶች ያመለክታሉ። በተጨማሪም በርካቶች ጥቃቱን ሽሽት ከመኖሪያቸው እየተፈናቀሉ በጎዳናዎች እና በጊዜያዊ መቆያ ስፍራዎች ተጠልለዋል።

የመካከለኛው ምሥራቅ ተደማጭ ሀገር የሆነችው ሳዑዲ አረቢያ በሊባኖስ ላይ እየተካሄደ ያለው ጥቃት በጣሙን እንዳሳሰባት እና የሀገሪቱ "ሉዓላዊነት እና የግዛት አንድነት እንዲከበር" ጥሪ በማቅረብ ከሊባኖስ ጎን እንደምትቆም ብታሳውቅም፤ የሐሰን ናስራላህ ግድያን በሚመለከት ግን ምንም ሳትል አልፋዋለች ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# በአዲሱ ዓመት እንደ ሄማን ያሉ ብላቴናዎች ይብዙልን

የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት ተፈጥሮም ጭምር የሚለወጥበት ነው፡፡ በመስከረም ወር መስኩ በልምላሜና በአበቦች ያጌጣል፤ አደይ ይፈነዳል፣ አዝመራው ያሸታል፣ ወንዞች ይጎላሉ፤ የደፈረሱት መጥራት ይጀምራሉ፣ ዝናብ ይቀንሳል፣ ተፈጥሮ ታጌጣለች፣ ሰማዩ ይጠራል፣ የመስቀል ወፎች ከተደበቁበት ይወጣሉ፡፡ ለዚህም ነው የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት የብሩህ ተስፋ መጀመሪያ ተደርጎ የሚታሰበው፡፡

ለአዲስ ዓመት በግልም በሀገር ደረጃም እናቅዳለን። እንመኛለን። እኔም የነገዋ ኢትዮጵያ ተስፋዎች የዛሬዎቹ ብላቴናዎች ናቸውና አዲሱ ዓመት የሰላም እንዲሆንላቸው እየተመኘሁ፤ በአዲሱ ዓመት እንደ ሄማን በቀለ ያሉ ብላቴናዎች እንዲበረክቱልን ከልብ እመኛለሁ። ለመሆኑ ታዋቂው የTIME መጽሔት እንደ አርአያ የመረጠው ሄማን በቀለ ማን ነው።

ሄማን በቀለ ገና የ7 ዓመት ብላቴና እያለ ነው የመድኃኒት ቅመማውን አሀዱ ያለው ይለናል የTIME መጽሔት ፀሐፊ ጄፍሪ ክሉገር። እስከ 10 ዓመቱ ድረስ የራሱን የሳይንስ ሙከራዎችን ሲያካሂድ ቆየ። እጁ የገባውን ሳሙና ይሁን ፈሳሽ ሳሙና እያደባለቀ ውጤቱን ይከታተላል። የእቃ ማጠቢያ ሳሙና፣ የላውንደሪ ፈሳሽ ሳሙና እና የተለመዱ የቤት ውስጥ የንጽህና ኬሚካሎችን በደመ ነፍስ እያደበላለቀ በአልጋው ስር ያሳድርና ማልዶ በመነሳት ውጤቱን ያያል። ይህ የዕለት ተዕለት ውሎው ሆነ።

የተወደዳችሁ የአዲስ ዘመን ቤተሰቦችና አንባቢዎች እንኳን ለ2017 አዲስ ዓመት አደረሳችሁ አደረሰን። አዲሱ ዓመት ሀገራችንና ሕዝባችን የናፈቃቸውን ሰላም የሚያገኙበት እንዲሆን በብርቱ እንመኛለን። በዛሬው መጣጥፌ ታዋቂውና ዝነኛው TIME መጽሔት የዓመቱ ብላቴና ስላለው ሄማን በቀለ ላስነብባችሁ ወደድኩ። ሄማን በሂደት ያገኘውን ሁሉ በዘፈቀደ ከመደበላለቀ እየተቆጠበ መጣ። ሰባተኛ ዓመት ልደቱን ቀድሞ የመጣው የፈረንጆች ገና ዕለት ከወላጆቹ የተበረከተለት የኬሚስትሪ ሙሉ ቁሳቁስና የሶዲየም ሃይድሮክሳይድ ናሙና ስጦታ የብላቴናውን ዕድሜ ቀጥፎት ነበር ይለናል ጄፍሪ።

ነገሩ ወዲህ ነው። ሄማን በዕለታት አንድ ቀን። ከትምህርት ቤት እንደተመለሰ እንደ ሁልጊዜው የኬሚስትሪ ሙሉ ቁሳቁሱንና ሶዲየም ሃይድሮክሳይዱ ወደሚገኝበትና እንደ ቤተ ሙከራ ወደሚጠቀምበት ክፍሉ ገብቶ አንዱን ኬሚካል ከሌላው እየቀላቀለ እያለ ድንገት እሳት ይፈጠርና ቃጠሎ ይነሳል። ሄመን ያን አጋጣሚ ሲያስታውስ እንዲህ ይላል። በእኔ ቤት ለዓለማችን የማይነጥፍ የኢነርጅ ምንጭ ለማግኘት እየሞከርሁ ነው። ሆኖም እሳት አስነስቼ እኔም ልቃጠል ቤቱም ሊጋይ ነበር ይላል።

ከእሳቱ በኋላ ወላጆቹ ከወትሮው በተለየ በቅርበት ይከታተሉት ጀመር። ሄማን ዛሬ 15 ዓመት የሞላውና የተረጋጋ ቢሆን በወላጆቹም ሆነ በሌሎች ክትትል ስር ሆኖ መሥራትን ተለማምዶታል ይለናል የTIME መጽሔት ፀሐፊ ጄፍሪ። አሁን አሁንማ ብዙ ሰዎች ለእሱ በጣም ትኩረት እየሰጡ ነው። ባለፈው ጥቅምት ወር 3M ኩባንያ እና የዲስከቨሪ ትምህርት በፌርፋክስ ካውንቲ ቨርጂኒያ በሚገኘው በውድሰን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ10ኛ ክፍል ተማሪ የሆነው ሄማንን የወጣት ሳይንቲስት አሸናፊ አድርጎ መርጦ 25,000 ዶላር ሸልሞታል።

የእሱ ግኝት ወደፊት ብዙ የቆዳ ካንሰርን ለማከም እና ለመከላከል የሚያስችል ሳሙና ለመፍጠር ጫፍ ላይ መድረሱ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ግኝት ወደ ገበያ ከመምጣቱ በፊት ዓመታት ሊወስድ ይችላል። ዛሬ ሄማን በገና በቤተሰቡ በተበረከተለት የኬሚስትሪ ቁሳቁስ ያደረገው የነበር የቤት ውስጥ ምርምሩ አድጎ በባልቲሞር በሚገኘው የጆንስ ሆፕኪንስ ብሉምበርግ የሕዝብ ጤና ተቋም ግዙፍ ቤተ ሙከራ ውስጥ የልጅነት ህልሙን ለማሳካት እየተጋ ነው።

ሄማን ለትምህርቱ ልዩ ትኩረት በመስጠትም ይታወቃል። ትምህርት ካለ በቤተ ሙከራ የሚያሳልፈው ጊዜ ይቀንሳል። ጊዜ ሲያገኝ ግን ብቅ ማለቱ አይቀርም። እሱም ሳይደብቅ በየአጋጣሚው ለቆዳ ካንሰር የተለየ ፍላጎት እንዳለው ይናገራል። አንድ ቀን የእኔ ምርምር ሆነ የሌሎች ምርምር ተሳክቶ የቆዳ ካንሰርን መከላከል ብሎም ማከም ሲቻል ከማየት በላይ የሚያስደስተኛ የለም። ለዚህ ነው ይሄን ምርምር የጀመርሁት ይለናል ህለመኛው ብላቴና ሄማን። ለዚህ ነው ሄማን የ2024 የዝነኛውና የተወዳጁTIME መጽሔት የዓመቱ ምርጥ ብላቴና የሚል እውቅና ያገኘው።

በዚህ ዕድሜው ባልተለመደ ሁኔታ ከራሱ ይልቅ ለሰው ልጆች ጤና መጨነቅ መጠበቡ ብዙዎች ታዋቂና ዝነኛ ሰዎች በሕይወታቸው የሚመኙትን የTIME የዓመቱ ሰው ሽልማትን ሊቀዳጅ ችሏል። ሄማን የተወለደው በአዲስ አበባ ሲሆን የአራት ዓመት ህጻን እያለ ከወላጆቹ ጋር ተሰደደ። የተሰደደው ግን ከማይረሳ የልጅነት ትውስታው ጋር ነበር። አዲስ አበባ የቀን ሠራተኞች በጠራራ ፀሐይ ያለ ምንም መከላከያ እንደሚሰሩ። ወላጆቹም እሱን ጨምሮ ታላቅ እህቱን ሀሴትንና ታናሹን ሊያን በፀሐይ መነጽር እንዲያደርጉና አለባበሳቸውንም እንዲያስተካክሉ መምከራቸው ለጉዳዩ የበለጠ ትኩረት እንዲሰጥ አስገድዷል።

ሄማን ይናገራል። ወደ አሜሪካ ስመጣ ረጅም ሰዓት ለፀሐይ ጨረር መጋለጥ ለተለያዩ የቆዳ በሽታዎችና ለካንሰር እንደሚዳርግ ይበልጥ በተገነዘብሁ ቁጥር የምርምር ፍላጎቴ እየጨመረ መጣ። የTIME መጽሔት ፀሐፊ ጄፍሪ ብላቴናው ሄማን በፀሐይ ጨረር የተነሳ ስለሚያጋጥመው የቆዳ ካንሰር ለመረዳት ብዙ ጊዜ አልወሰደበትም ይለናል። ከጥቂት ዓመታት በፊት ኢሚኩሞድ ስለተሰኘ የቆዳ ካንሰር መድኃኒት ቢያነብም። ህክምናው ከ40ሺህ ዶላር በላይ ይጠይቃል። ዋጋው የማይቀመስ ስለሆነ ለድሆች በቀላሉ የማይደርስ መሆኑን ሲያውቅ ይበልጥ በተመጣጣኝ ዋጋ ለሁሉም ተደራሽ የሚሆን መድኃኒት ስለማግኘት ሌት ተቀን ማሰብ ጀመረ።

ሄማን "ዓለም አቀፍ ተጽዕኖ ሊፈጥር የሚችል እና ሁሉንም ሰው ተጠቃሚ ሊያደርግ ስለሚችል ሃሳብ ሲያንሰላስል ወደ አእምሮው ቀድሞ የመጣለት፤ ሀብታም ድሀ፣ ነጭ ጥቁር ሳይለይ ሁሉም በቀላሉ ሊያገኘው የሚችል የቆዳ ካንሰር መከላከያና መድኃኒት ሳሙና መፍጠር ነበር ይለናል ተነባቢው TIME መጽሔት። ሄማን ምርምሩን ዳር ለማድረስ ገና ብዙ ፈተና እንደሚጠብቀው ጄፍሪ ሲያትት በራዕይና በትግበራ መካከል ረጅም መንገድ አለ ይለናል።

ሄማን ይለናል ፀሐፊው ለቆዳ ካንሰር መድኃኒት ለማግኘት የሚያደርገው ጥረት የብዙዎችን ትኩረት እየሳበ ነው። የብላቴናው ምርምር ቀልቡን ከሳባቸው ኩባንያዎች 3M የተባለ ኩባንያ ቀዳሚው ነው። እያደረገ ስላለው ምርምር አላማና ግብ ገለጻ እንዲያደርግለት ጋብዞት ነበር፤ እሱም ገለጻውን ከሸኖ በቪዲዮ ላከ። ብዙም ሳይቆይ፣በሴንት ፖል፣ ሚኒ በሚገኘው የኩባንያው ዋና መሥሪያ ቤት የምርምር ሃሳቡን በአካል ዳኞች ለማቅረብ ግብዣ ተቀበለ። ከዚህ በፊት አሸናፊ ተብሎ መመረጡና የ25,000 ዶላር ሽልማት ማግኘቱ አይረሳም። ነገር ግን አሁንም ድጋፍና እገዛ ይፈልጋል። ለምርምሩ የሚመጥን የተሟላ ቤተ ሙከራ ይፈልጋል።

በዚሁ ዓመት ወርሀ የካቲት ላይ በሜላኖማ ሪሰርች አሊያንስ በዋሽንግተን ዲሲ በተዘጋጀው የበይነ መረብ ውይይት ላይ እየተሳተፈ ሳለ የሞለኪውላር ባዮሎጂስት እና ባልቲሞር በሚገኘው የጆንስ ሆፕኪንስ ረዳት ፕሮፌሰር ከሆነችው ቪቶ ሬቤካ ጋር ተዋወቀ። ሬቤካ አጋጣሚውን እንዲህ ታስታውሰዋለች። "ስለዚህ ህልመኛ ብላቴና የቆዳ ካንሰር መከላከያና ማከሚያ ሳሙና የምርምር ሃሳብ ያወቅሁት ዛሬ በውል ከማላስታውሰው አንድ ንባቤ ነው። ወዲያው ፍላጎቴን አነሳሳኝ፣ ምክንያቱም እሱ ከራሱ ይልቅ ለሰዎች የሚጨነቅ ብላቴና ነው። መድኃኒቱን ተሳክቶለት ቢያገኝ በተመጣጣኝ ዋጋ ለሁሉ እንዲደርስ ነው የእሱ ምኞት።

ከዚያ፣ በሜላኖማ ምርምር ሕብረት ስብሰባ ላይ የህብረቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ከሄማን ጋር አስተዋወቀኝ። ከዚህ በኋላ ነጮች እንደሚሉት ቀሪው ታሪክ ነው። the rest is history ትለናለች። ሬቤካ በምርምሩ ልታግዘው፣ ስፖንሰሩ ልትሆነውና በባልቲሞር የሚገኘውን እጅግ ዘመናዊ የሆነውን ቤተ ሙከራቸውን ደግሞ በነፃነት እንዲጠቀም ፈቀደችለት። ላለፉት ስድስት ወራት ፕሮፌሰር ሬቤካና ሄማን ምርምሩን በጋራ እያካሄዱ ነው። አይጦችን የቆዳ ካንሰር ህመም ይወጉና ከዚያ በሙከራ ላይ ያለውን መድኃኒታቸውን ይሰጡና ውጤቱን በትኩረት ይከታተላሉ ይለናል የTIME መጽሔት ፀሐፊ።

ግኝታቸው ወደ ተሟላ ሙከራ ሊገባ ጫፍ የደረሰ ቢሆንም ሄማን ግን ገና ብዙ እንደሚቀረው አምኖ የሥነ ልቦና ዝግጅት አድርጓል። ሙከራው ውጤታማ ቢሆን እንኳ ከአሜሪካ የምግብና የመድኃኒት ባለሥልጣን FDA ፓተንት ማግኘቱ ራሱ አስርት ዓመታትን ሊወስድ እንደሚችል የልጅ አዋቂው ሄማን ይረዳል። ለነገሩ ይለናል መልሶ ፀሐፊው ጄፍሪ ሄማን ተሳክቶለት በሚቀጥሉት 10 ዓመታት ውስጥ የቆዳ ካንሰር መድኃኒቱ ፓተንት ቢያገኝለት እድሜው ገና የ25 ዓመት ወጣት ነው። የሜዲካል ተማሪዎች የድህረ ምረቃ ዲግሪያቸውን ሳይጨርሱ ሄማን የቆዳ ካንሰርን የሚከላከል መድኃኒት የፓተንት ባለቤት ሆኗል። ጊዜውን በአግባቡ እየተጠቀመ ነው።

ሄማን በዚህ ለጋ እድሜው ተመራማሪ መሆኑ ብቻ አይደለም የሚያስገርመው ስለ ቆዳ ካንሰርም ሆነ ስለ ምርምሩ ሰፊ የማስተዋወቅ ሥራ እየሰራ ነው። ባለፈው ሰኔ በቦስተን በሚገኘው ቶንጋስ ማዕከል በተሰባሰቡ 800 አንቱ የተባሉ ሐኪሞችና ሳይንቲስቶች ፊት ቀርቦ የምርምሩን ሂደት አስተዋውቋል። ያስፈራ ነበር ግን ደግሞ አስደሳችም ነበር ሲል በወቅቱ የተፈጠረበትን ድብልቅልቅ ስሜት ገልጾታል።

በነገራችን ላይ ሄማን ከምርምሩና ከቤተ ሙከራ ውሎው ባሻገር የትምህርት ቤቱ ውድሰን 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ማርች ባንድ ዋሽንትና ትሮምቦን ተጫዋች ነው። አንባቢና ቅርጫት ኳስ ተጫዋችም ነው። ሄማን ለዚህ ስኬት ያበቁትን ወላጆቹን አመስግኖና ስማቸውን አንስቶ አይጠግብም። መምህርት የሆኑትን እናቱን ወ/ሮ ሙሉእመቤትና በአሜሪካ የዓለም አቀፍ ልማት ተቋም የሰው ኃይል ተጠሪ ሆነው የሚሰሩትን አባቱን አቶ ወንድወሰን ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ያመሰግናል። ለእሱ የከፈሉትን መስዋዕትነት ያነሳል። አመስጋኙ ብላቴና መች በዚህ ሊያቆም ተባባሪ ተመራማሪዋን ፕሮፌሰር ሬቤካን፤ ምሳሌና መካሪውን ወይም ሜንተሩን እንዲሁም የ3M ባልደረባ ዲቦራህ ኢዛቤሌን እንዲሁ ያመሰግናል።

ስለ ሄማን የተጠየቀችው ሜንተሩ ዲቦራህ የእሱ ሜንተር በመሆኔ ሲበዛ እድለኛ ነኝ። ባለፈው ዓመት ነበር ወጣት ሳይንቲስቶችን በሚያግዘው ቻሌንጅ ከሄማን ጋር የተጣመርሁት። በእውነቱ የሚገርም ተወዳጅና አነቃቂ ብላቴና ነው።ይህን ስል ሄማን ፍጹም ነው። አይሳሳትም። ሙሉ በኩልዬ ነው እያልሁ አይደለም። እንደ ማንኛውም ህጻን ያጠፋል። ይሳሳታል። ሲሳሳት አርመዋለሁ። ከጎኑ ቆሜ ሊወድቅ ሲል እደግፈዋለሁ።

በዕለታት አንድ ቀን ስትል ዲቦራህ ኢዛቤሌ ሄማን የሳተውን ነገር መለስ ብላ ታስታውሳለች። ቤተ ሙከራ ውስጥ የቆዳ ካንሰር ሳሙናውን እያዘጋጀ ሳለ ያልተጠበቀ ነገር ተከሰተ። ምንድን ነው የሆነው፤ እንዴት እንዲህ ሊሆን ቻለ ብዬ ስጠይቀው። ቅደም ተከተሉንና መመሪያውን ሳይከተል ሳሙናውን ለማዘጋጀት መሞከሩ ለስህተት እንደዳረገው ሳይደብቅ ነገረኝ። ከዚያ እንዲያስተካክል ተነጋገርንና ስህተቱን አረመ። ከስህተቱም እንደተማረ ነገረኝ።

ይህ የመውደቅ መነሳት፣ደጋግሞ የመሞከር ጥረት ነው የሄማንን የቆዳ ካንሰር መከላከያን ወይም ያልተስፋፋ ካንሰርን ወይም ደረጃ ዜሮ የሆነን ካንሰር መድኃኒትን እውን የሚያደርገው ትለናለች ሜንተሩ። ገና በ15 ዓመቱ ዝነኛና ታዋቂ ብላቴና ቢሆንም ሄማን ዛሬም ትሁትና ከራሱ ይልቅ ሰዎችን የሚያስቀድም የዋህ ነው። ሰዎች ሲያደንቁትና ሲያሞካሹት ሄማን በትህትና እኔ የማደርገውን ማንም ሊያደርገው ይችላል። የተለየ ያደረግሁት ነገር የለም። ህልምና ራዕይ ይዤ ተነሳሁ። ወደዛ የሚያደርሰኝን መንገድ ተከተልሁ። ዛሬ ላይ ደረስሁ ይለናል።

ሄማን ይሄን ይበል እንጂ። ስጋቱን አይሸሽግም። በህክምና፣ በምህንድስና እንዲሁም በሰው ሠራሽ አስተውሎት ሳይንሳዊ ግኝቶች ወዲያው ወዲያ እየወጡ ስለሆነ ዘርፉ እንዳይጨናነቅ ይፈራል። በርግጥ ፍርሀቱ በፍራት ላይ ያነጣጠረ ነው። የሰው ልጅ ችግሮች አብረውት የሚኖሩና ተለዋዋጭ በመሆናቸው እና ፍላጎቱም ማቆሚያ ስለሌለው ሄማን ስጋት ሊገባው አይገባም የሚሉ አሉ።

ሻሎም።አሜን።

# ስፖርት

# አዳዲሶቹ የበርሊን ማራቶን ከዋክብት

ብርሃን ፈይሳ

በአትሌቲክስ ታሪክ በርካታ የማራቶን የዓለም ክብረወሰኖችን ከተመዘገቡባቸው ውድድሮች መካከል ግንባር ቀደሙ የበርሊን ማራቶን ነው፡፡ ዘንድሮ 50 ዓመቱን ያከበረው ይህ የፕላቲኒየም ደረጃ የተሰጠው ውድድር ባለፉት ዓመታት 13 የዓለም ክብረወሰኖች የተሰበሩበት ነው፡፡ የበርሊን ማራቶን ከተመሰረተበት ጊዜ አንስቶ ባለፉት በርካታ ዓመታት የአሸናፊነት መንበሩን መቆጣጠር የቻሉት ምስራቅ አፍሪካውያኑ የኬንያ እና ኢትዮጵያ አትሌቶች ሲሆኑ፤ ላለፉት 11 ዓመታት ደግሞ የዓለም የምንጊዜም ምርጦቹ የረጅም ርቀት አትሌቶች ቀነኒሳ በቀለ እና ኢሉድ ኪፕቾጌ ፉክክሩን ወደ ላቀ ደረጃ አሸጋግረውታል፡፡

በርሊን ማራቶን 50ኛ ዓመቱን ከትናንት በስቲያ እያከበረ የዘንድሮውን ዓመት ውድድር ሲያካሂድ ከዚህ ቀደም በተለየ ሁኔታ ወጣትና ለማራቶንም አዲስ ሊባሉ የሚችሉ አትሌቶች ደምቀውበታል፡፡ በጀርመኗ መዲና በጸሃያማው ዕለት በተከናወነው በዚህ ውድድር ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በሁለቱም ፆታ በአሸናፊነት አጠናቀዋል፡፡



የበርሊን ማራቶን አሸናፊዎቹ ሚልኬሳ መንገሻ እና ትዕግስት ከተማ፤

በወንዶቹ መካከል በተካሄደው ውድድር አትሌት ሚልኬሳ መንገሻ አሸናፊ ሲሆን ፉክክሩን ያተናቀቀበት ሰዓትም 2:03:17 ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ይህም ለአትሌቱ የርቀቱ የግሉ ፈጣን ነው፡፡ ከመም ውድድር እአአ በ2022 ወደ ጎዳና ላይ ሩጫዎች የገባው ሚልኬሳ ባለፈው ዓመት በዴጉ ማራቶን አሸናፊ በመሆን ነበር ያጠናቀቀው፡፡ በዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮናም 6ኛ ደረጃን በመያዝ ነበር የፈጸመው፡፡ በተያዘው ዓመት የሂውስተን ግማሽ ማራቶን እንዲሁም አሜሪካ በተካሄደ የ 10 ኪሎ ሜትር ውድድር በመሳተፍም የውድድር ዓመቱን አሳልፏል፡፡

ከጅምሩ ፈጣን በነበረው የዘንድሮው በርሊን ማራቶን የርቀቱ ግማሽ በአሯሯጮች የታገዘ ቢሆንም እስከ 30ኛው ኪሎ ሜትር ድረስ ከኬንያ እና ኢትዮጵያውያን አትሌቶች መካከል አሸናፊ የሚሆነውን መለየት አስቸጋሪ ነበር፡፡ በተለይም በኢትዮጵያዊው የውድድሩ ፈጣን አትሌት ታደሰ ታከለ እና የቀድሞ የዓለም ግማሽ ማራቶን ቻምፒዮን ኬንያዊው ኪብዎት ካንዳይ መካከል የነበረው ፉክክር ጠንካራ የሚባል ነበር፡፡ እስከ 41ኛው ኪሎ ሜትር ድረስም ከሚልኬሳ ውጪ ደጀኔ መገርሳ፣ ሃይማኖት አለው እና ስቴፈን ፒፕሮፕ የመሳሰሉ አትሌቶች የተሻለውን የአሸናፊነት ግምት ያገኙ ነበሩ፡፡ 41 ኪሎ ሜትሩን ያገባደዱትም በ1:56:59 ሰዓት ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ከዚያ በኋላ ያሉትን ኪሎ ሜትሮችም በሚልኬሳ የበላይነት የተሸፈነ ሲሆን፤ በዚህ ዓመት በማራቶን ከተመዘገቡ ሰዓቶች ፈጣኑ እንዲሁም አትሌቱ ከነበረው ሰዓት በ2 ደቂቃዎች ፈጥኖ በመግባት አሸናፊ ሊሆን ችሏል፡፡ ሁለተኛ የሆነው ሳይብሬን ኮቱት 2:03:22 በሆነ ሰዓት ተከትሎት ሲገባ፤ ሃይማኖት አለው ደግሞ 2:03:31 በሆነ ሰዓት ሶስተኛውን ደረጃ ይዟል፡፡

በሴቶች መካከል በተካሄደው ውድድር አስቀድሞ የአሸናፊነት ግምት የተሰጣት ትዕግስት ከተማ የሀገሯን ልጆች አስከትላ በመግባት ፉክክሩ በኢትዮጵያውያን የበላይነት ተጠናቋል፡፡ ያለፈው ዓመት የዱባይ ማራቶን አሸናፊዋ አትሌት በለንደን ማራቶን 7ኛ ደረጃን በመያዝ ነበር ያጠናቀቀችው፡፡ ሆኖም የ26 ዓመቷ አትሌት ያላት ሰዓት በዚህ ውድድር ከተሳተፉ አትሌቶች መካከል ቀዳሚውን ደረጃ የያዘ ነበር፡፡ ዓምና በበርሊን የሴቶች የዓለም ክብረወሰንን ያስመዘገበችው ሌላኛዋ ኢትዮጵያዊት አትሌት ትዕግስት አሰፋ ጋር የምትሠለጥነው አትሌት ትዕግስት ከተማ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ጋር በመሆን ውድድሩን በመቆጣጠርም ነበር የሮጠችው፡፡ ከ40 ኪሎ ሜትር በኋላም ከተፎካካሪዎቿ ጋር የ2 ደቂቃ ልዩነት በመፍጠር በመሮጧ 2:16:42 በሆነ ሰዓት ውድድሩን በአሸናፊነት ለማጠናቀቅ አስችሏታል፡፡

የዚህ ዓመት የፓሪስ ማራቶን አሸናፊዋ እና በዚህ ውድድርም ጠንካራ ፉክክር ያደረገችው መስታወት ፍቅር በሁለት ደቂቃ ዘግይታ በመግባት ቀጣዩን ደረጃ ይዛለች፡፡ በ10ሺ ሜትር የምትታወቀው በሰና ሙላቴ እና አበሩ አያና ደግሞ በሶስተኛ እና አራተኛ ደረጃ ውድድሩን ደምድመዋል፡፡